በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት የተዘጋጀ

ካገረ ማርያም (ካማ 311)

አዘጋጅ፡- መ/ር ሰሎሞን

፳፻፷ ዓ.ም

መግቢያ

በነገረ ድህነት ትምህርት ውስጥ “ምክንያተ ድህነት” የሆነችውን የእመቤታችንን ነገር ማወቅና መረዳት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ተወለደ ሰው ሆነ ስንል እንዴት ሰው ሆነ የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ስለሆነ ነው፡፡ ከአዳም መርገም በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት ተጠብቃ የቆየች መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የነገራትን ቃል በፍፁም እምነት ተቀብላ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ በማለትዋ እግዚአብሔር ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ፍፁም ሰው በመሆን እናት ትሆነው ዘንድ የመረጣት ሰዎችን ለማዳን ባደረገው ጉዞ ውስጥ ሁሉ መከራን ተቀብላ ያገለገለች ስለሆነ ስለ እመቤታችን መማር ነገረ ድኅነትን ለመረዳት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህም በላይ ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ስለሆነች ሰዎች ነገረ ድህነትን አምነው በምግባር ለመኖር ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በሚያደርጉት ተጋድሎ ውስጥ ረዳት ምርኩዝ ልትሆናቸው የተሰጠች ስለሆነ አማላጅነትን ጸጋዋን በረከትዋን እየተማፀኑ መኖር የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን የነገረ ድኅነት አስተምህሮ አካል ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የትምህርተ ክርስትና መግቢያ ትምህርተ ሃይማኖት ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባርንና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ከተማሩ በሁዋላ የነገረ ማርያምን ትምህርት ይማሩ ዘንድ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ይህንን ትምህርት ተማሪዎቹ እመቤታችን ነገረ ድህነት ያላትን ቦታ እንዲገነዘቡ ቅድሳናዋን አማላጅነትዋንና በረከትዋን ትንቢቶችና ምሳሌዎች እዲረዱና በረከትዋን ቃል ኪዳንዋን አምነው የበለጠ እንዲጠቀሙ ከማድረግ አንፃር ይህ መፅሐፍ ተዘጋጅቷል፡፡

መፅሐፍም በውስጡ አምስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ምዕራፍ አንድ የነገረ ማርያም ትምህርት መሰረታዊያን የሚል ሲሆን በውስጡ ነገረ ማርያም ማለት ማለት ነው ?መማር ለምን አስፈለገ የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጭ ምንድነው ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡ምዕራፍ ሁለት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልደት ጀምሮ በአጠቃላይ የህይወት ታሪኳን የሚናገር ሲሆን ምዕራፍ ሦስት ደግሞ ነገረ ማርያም በነገረ ድኅነት የሚል አቢ ርዕስ ሲኖረው በውስጡም በሰው ልጆች መዳን እመቤታችን ያላትን ሱታፌ ጥንተ አብሶ የሌለባት መሆኑን እና ከጌታ ፅንስእስከ ቀራኒዮ እመቤታችን ያደረገችውን አገልግሎት የእመቤታችን ምልጃ በነገረ ድህነት ምን እንደሚመስል በስራው ያትታል ምዕራፍ አራት ክብረ ድንግል ማርያምን የሚገልፅ ሲሆን በዚህም ውስጥ ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆኗ ቅድስናዋ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋ ስግደት እና ምስጋና የሚገባት መሆኑ በሰፊው ተገልፆአል፡፡በምዕራፍ አምስት ደግሞ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአበው ቀደምት የተመሰሉ ምሳሌዎች እና በቅዱሳን ነቢያት የተነገሩት ትንቢቶች የሚገለፁበት ሰፊ ክፍል ይዟል፡፡በስተ መጨረሻም የነገረ ማርያም ትምህርት ማጠቃለያ ተዕፎለታል፡፡ ከዚያም ዋቢ መፃህፍት ተገልፀዋል፡፡

ነገረ ማርያም በሚል ርእስ በአዲስ መልክ የተዘጋጀው ይህ የመማሪያ መፅሐፍ ማህበረ ቅዱሳን አዲስ በከለሰው ሥርዓተ ትምህርት መሰረት የተሰናዳ ነው፡፡ አገልግሎቱ በዋናነት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላሉት የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ሲሆን የኢትዮጲያ ሶርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲን እምነት ተከታዮች ለሆኑ ምዕመናን በሙሉ እንዲጠቅም ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን አሜን

ነገረ ማርያም

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ወይም ነገረ ማርያም የተሰኘውን ትምህርት ለምን መማር እንዳስፈለገ እና የትምህርቱን የት መጣውን የምንማርበት ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት የነገረ ማርያም መሰረታውያን የሆኑትን ማለትም ነገረ ማርያም

- ማለት ምን ማለት ነው?
- ነገረ ማርያምን መማር ለምን አስፈለገ?
- የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች ምን ምን ናቸው?

የሚሉትን የምናትትበት ነው። በዚህ ክፍለ ትምህርት ተማሪዎቹ የነገረ ማርያምን መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ይረዳሉ።ነገረ ማርያም ምን ማለት እንደሆነ ይገነዘባሉ።

ጥያቄ

ሀ.ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?አብራራ (ሪ)

ለ.የነገረ ማርያም ትምህርት መማር ጥቅሙ ምንድን ነው?

ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?

ከሁለት ቃላት የተገኘ /የተሰናሰለ/ ሲሆን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ንፅህና፣ቅድስና፣ዘለዓለማዊ ድንግልና ወ.ዘ.ተ የምንማርበት እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሰው ልጆች መዳን ውስጥ(በነገረ ድህነት) ያላትን ሱታፌ (አስተዋጽኦ) የምንረዳበት የትምህርት ክፍል ነው።

ነገረ ማርያምን መማር ለምን አስፈለገ?

ሀ.ክርስትናን በአግባቡ ለመረዳት፦ ክርስትና አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጦ የመሰረታት ናት ቅድመ ዓለም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል ሆኖ ዓለምን የፈጠረ እና የሚገዛ እግዚአብሔር ቃል (ወልድ) ድህረ ዓለም የጠፋውን አዳምን ፍለጋ በትሕትና እራሱን ዝቅ አድርጎ በሰው ባህርይ መገለጡን ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው መሆኑን የምናምንበት የምንረዳበት ትምህርት ነው።በዚህ በነገረ ድህነት የክርስትና ትምህርት ሰፊውን ድርሻ ይዛ የምትገኘው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዓለም ሁሉ ለዳነበት ምስጢር መፈጸሚያ መቅደስ ለመለኮት ማደሪያ እንድትሆን ተመርጣለች።በሰዎች ላይ ሰልጥኖ የነበረው የጨለማው ገዢ ዲያብሎስ ድል የተነሳበት አዳም ከጨለማ ግዞት ነፃ የወጣበት አማናዊ ብርሃን

ፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገኘባት ምስራቅ የድህነታችን መሰረት የመዳናችን ምክንያት በመሆኗ ነገረ ማርያምን ትምህርት መማር አስፈልጓል።

ለ.<u>ስለ እመቤታችን ፀጋ እና ክብር ለማወቅ</u>፦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአምላካችን ከልዑል እግዚአብሔር በተሰጣት ፀጋ ከነገደ መላእክት ከደቂቀ አዳም በክብር የሚመስላት በፀጋ የሚተካከላት የለም ይኸውም ከፍጡራን መካከል ተለይታ የአምላክ እናት ለመሆን የተመረጠች አምላክን በህቱም ድንግልና ፀንሳ በህቱም ድንግልና የወለደች ሁሉን የሚመግበውን አምላክ ጡቶቿን አጥብታ ያሳደገች በጀርባዋ ያዘለች ስለ ልጇ የተሰደደች በማለት ማስተማር ዘመኑ ከጌታችን ጋር የነበረች እስከ እግረ መስቀል ያልተለየች በመሆኗ ስለ እርሷ ስለተሰጣትም ፀጋ እና ክብር ለማወቅ አውቆም ለማክበር ነገረ ማርያም ትምህርት መማር ያስፈልጋል።

ሐ.<u>በሕይወታችን ለመጠቀም</u>፦ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጣት የከበረ ቃል ኪዳን አለ ቃልኪዳኑም "ስምሽን የጠራ ዝክርሽን የዘከረ በቃል ኪዳንሽ የታመነውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ አድነዋለሁ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እሰጠዋለሁ" የሚል ነው።ይህ ቃል ኪዳን በህይወታችን እንዲሰራ በነፍስም በሥጋም ከኃጢአት በስተቀር የምንፈልገውና የሚገባን (የሚጠቅመን) ነገር እንዲፈፀምልን ይህንን የምናውቅበትን እና የመንረዳበትን ትምህርት ነገረ ማርያምን መማር ያስፈልጋል።

<u>የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች</u>

የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጭ አለው የነገረ ማርያም ትምህርት ልብ ወለድ ፈጠራ ሳይሆን ምንጭ አለው ምንጩም የመንፈሳውያን መፃህፍትና ትምህርት መሰረታቸው የሆነ መፅሐፍ ቅዱስ ነው። ይኸውም በሁለት የተከፈለ ነው "ብሉይ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳን" በዚሁ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን የእመቤታችን ነገር በዘመነ ብሉይ በአበው ቀደምት ምሳሌ በነቢያት ትንቢት የተገለጠ በዘመነ ሐዲስ በሐዋርያት ስብከት ፍፃሜውን አግኝቶ የተሰበከ በመሆኑ ቅዱስ መፅሐፍ የነገረ ማርያም ምንጭ ነው።

ከመፅሐፍ ቅዱስ ቀጥሎ የነቢያትን የሐዋርያትን አሰረ ፍኖት ተከትለው ሊቃውንት በድርሰታቸው የእመቤታችንን ነገር ገልጠው ፅፈዋል በተለይ በጊዜው ከተነሱ መናፍቃን ለክህደት ትምህርታቸው መልስ ለመስጠት ባዘጋጁት በሃይማኖተ አበው የነገረ ማርያም ትምህርት የተገለጠ በመሆኑ ለነገረ ማያርም ትምህርት ምንጭ ሆኗል።

ከዚህ በተጨማሪ ለነገረ ማርያም ትምህርት ምንጭ የሚሆኑ ተአምረ ማርያም፣የቅዱስ ያሬድ የድጓ ድርሰት፣የአባ ጊዮርጊስ ድርሰቶች ማለትም፦እነ አርጋኖን ዘእግዝእትነ ማርያም፣እነ ሆሕተ ብርሃን፣እነ እንዘራ ስብሐት፣መዓዛ ቅዳሴ የአባ ሕርያቆስ ቅዳ የቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ ወ.ዘ.ተ።ያሉ

ድርሰቶች ናቸው።እነዚህን ድርሰቶች ያስደረሳቸው እና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ነገር የገለፀላቸው ያደረባቸው እና የመረጣቸው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው።መንፈስ ቅዱስ ያላደረበት የእመቤታችን ክብር ገልፆ መናገር አይችልምና።(ሉቃ 1፥39)።በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ መላባት ድምጿን ከፍ አድርጋ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው.....።አለች" እንዲል።

ማጠቃለያ

የነገረ ማርያም ትምህርት መግቢያ የሚሆን ነገረ ማርያም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ነገረ ማርያምን ትምህርት መማር ክርስትናን በአግባቡ ለመደራት ስለ እመቤታችን ፀጋ እና ክብር ለማወቅ እንዲሁም በእመቤታችን ምልጃ በቅድስና ህይወት በህይወታችን ለመጠቀም ብሎም የነገረ ማርያም ትምህርት ምንጮች መፅሐፍ ቅዱስና እና ሌሎች አዋልድ መፃህፍት መሆናቸውን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡በይበልጥ ደግሞ በነገረ ማርያም ዙሪያ የተፃፉ ነገሮችን ማንበብ ይረዳል፡፡

ዋቢ መፃሕፍት

1.መፅሐፍ ቅዱስ

2."ወላዲተ አምላክ" በመፅሐፍ ቅዱስ ቀሲስ ደጀኔ ቀሲስ እሸቱ

3."ነገረ ማርያም" ማኅበረ ቅዱሳን ት.ሐ.አ.

ምዕራፍ ሁለት

<u>የእመቤታችን ታሪክ</u>

<u>መግቢያ</u>

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የዘር ሐረግ፣ከማን ወገን እንደሆነች ፣ እንዴት እንደተወለደች እና በቤተ መቅደስ የአስተዳደጓን ሁኔታ እንዲሁም ከቤተ መቅደስ በዘመኑ ከነበሩ ሽማግሌዎች መካከል በተለያየ አይነት ምልክት ተመርጦ አረጋዊ ዮሴፍ እመቤታችንን እንዲጠብቃት መሰጠቱና በቅዱስ ገብርኤል አብሳሪነት ጌታን በሀቱም ድንግልና ፀንሳ በሀቱም ድንግልና መውለዷ ከጌታችን ጋር 33 ዓመት ከሦስት ወር መኖሯ ከጌታችን በኋላ ከሐዋርያት ጋር መኖሯ ብሎም ከዚህ ዓለም ድካም በ64 ዓመቷ በ49 ዓ.ም ገደማ ማረፏ እና አይሁድ በክፋት ሥጋዋን ሊያቃጥሉ ሲመጡ በተደገረ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት የእመቤታችን ሥጋ መሰወሩ እና በሀዋርያት ፆም እና ፀሎት መገለጡ በስተመጨረሻም የእመቤታችን ትንሣኤ እና እርገት የሚነገርበት ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የስሟ ትርጓሜ ከብዙ በጥቂቱ ለማሳያ ያህል ተገልያል፡፡በአጠቃላይ በምዕራፍ ሁለት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክ የምንማርበት ነው፡፡

<u>ጥያቄ</u>

ሀ.የእመቤታችን የትውልድ ሐረግ ዘርዝር

ለ.የእመቤታችን ልደትና የአስተዳደግ ሁኔታ አብራራ

ሐ.የእመቤታችንን ስም ማርያም የሚለውን ግልፅ

መ.የእመቤታችንን ዘይቤያዊ ስሞች ***<u>ለምሳሌ</u>***፦ “ *ኪዳነ ምህረት* ” ሌሎችንም ግለፅ እና አብራራ

<u>የእመቤታችን ታሪክ</u>

<u>2.1.የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም</u>

<u>የልደቷ ታሪክ</u>

“የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር”። (ኢሳ 1፥9)።ይህ ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ የተናገረው ቃል ምስጢር አዘል ሲሆን የተነገረውም ለወላዲተ አምላክ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ነው።ነቢዩ በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝቶ እንደተናገረ ስለ አዳም ልጆች መዳን ያስቀራት ንፅሕት ዘር ማለትም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።በሌላም

ሥፍራ ቅዱስ ዳዊት ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የልደቷ ነገር ሲገልፅ እንዲህ አለ ።(መዝ 86፥1)።“መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱስን (መሠረቶቿ የተቀደሱ ተራሮች ናቸው)።”ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት መሰረቶቿ የተቀደሱ ተራሮች ናቸው ብሎ ከአዳም ጀምሮ እነ አብርሃምን እነ ዳዊትን እነ ሰሎሞንን ወ.ዘ.ተ እስከ ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሃና ያሉትን በምስጢር ማንሳቱ ነው።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የልደቷን ታሪክ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።በኢየሩሳሌም አካባቢ በቅዱስ ጋብቻ ተወስነው እግዚአብሔርን እያመለኩና እያመሰገኑ የሚኖሩ ጳጥርቃና ቴክታ የሚባሉ ደጋግ ሰዎች ነበሩ።ይሁን እንጂ ልጅ የሌላቸው መካኖች በመሆናቸው ያፈሩትን ሀብት የሚወርስ ልጅ ባለመውለዳቸው ያዝኑ ይተክዙ ነበር።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ስለ ሀብታቸው ብዛት በሰፊው ከተወያዩ በኋላ ጳጥርቃ ተስፋ በመቁረጥ ስሚ “እህቴ ሆይ ይህ ሁሉ የሰበሰብነው ገንዘባችንን ምን እናደርገዋለን የሚወርሰን ልጅ የለንም ምክንያቱም አንቺ መካን ነሽ እኔ ደግሞ ከአንቺ በቀር ሌላ ሴት አላውቅም።አላት ቴክታም “ጌታዬ ሆይ አምላክ እስራኤል ለእኔ ልጅ ቢነሳኝ አንተም እንደ እኔው ትቀራለህን ከሌላ ውለድ እንጅ?” ብላ ብታሰናብተው እርሱም “እንዲህ ያለ ነገር እንኳንስ ላደርገው በልቡናዬ እንደማላስበው አምላክ እስራኤል ያውቃል”አላት።

ከዚህ ሁሉ ውይይት በኋላ ቴክታ ለጳጥርቃ እንዲህ አለችው እግዚአብሔር የሚያደርገውን የሚያውቅ የለም ትላንትና ማታ በሕልሜ ነጭ ጥጃ ከማህፀኔ ስትወጣ ያችም ነጭ ጥጃ ሌላ ነጭ ጥጃ ስትወልድና እስከ ሰባት ትውልድ ድረስ ሲዋለዱ ሰባተኛይቱ ጨረቃን ስትወልድ ጨረቃ ፀሐይን ስትወልድ አየሁ አለችው በዚህ ተደንቀውና እግዚአብሔርን አመስግነው ወደ ሕልም ፈች ዘንድ ሂደው የሆነውን ሁሉ ነገሩት ያም ሕልም ፈች እግዚአብሔር በምሕረቱ አይቷችኋል በማህሉ መግቧችኋል ብሎ ሕልማቸውን እንዲህ ሲል ፈታላቸው።

ሰባት እንስታት ጥጆች መውለዳቸው ወይም ሲወለዱ ማየታቸው ሰባት ሴት ልጆች ትወልዳላችሁ ሰባተኛይቱ ጨረቃን መውለዷ ከሰው የበለጠች ከመላእክት የከበረች ደግ ፍጥረት ትወልዳላችሁ የፀሐይ ነገር ግን አልተገለፀልኝም ጊዜ ይፍታው አላቸው።በዚያም ወራት ቴክታ ፀነሰች ሴት ልጅ ወለደች ስሟን ሄሜን ብለው አወጡላት በመቀጠልም የሚከተሉት በተከታታይ ተወለዱ።

ሄሜን ዴርዴን ወለደች ዴርዴም ቶናን ወለደች ቶናም ሲካርን ወለደች ሲካርም ሴትናን ወለደች ሴትናም ሄርሜላን ወለደች ሄርሜላም ማጣትን አግብታ ከአንስት ዓለም ተመርጣ የአምላክ አያት ለመሆን የበቃችውን ቅድስት ሐናን መስከረም 7 ቀን ወለደች ሐናም በሥርዓት አደገች

ለአካለ መጠን ስትደርስ ከቤተ መንግሥት የተወለደውን ክቡር ፃድቅ የሆነ ኢያቄም የሚባለውን ሰው አጋቢት።

በዚህ በተቀደሱ አባቶችና እናቶች የዘር ሐረግ ውስጥ አልፈው የመጡት ቅዱስ ኢያቄም እና ቅድስት ሃናም እግዚአብሔር ለድህነተ ዓለም የመረጣት ቅድስት ድንግል ማርያምን ወለዱ።በነገረ ማርያም እንደተፃፈ ቅዱስ ኢያቄም እና ቅድስት ሃና የፃድቃን መሰረቶች ቢሆኑም ከዚህ ዓለም ብዕል ግን ድሆች ነበሩ ምንም ድሆች ቢሆኑም ፍቅራቸው ወደር የሌለው አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ተባብለው የሚኖሩ ደጋግ ባልና ሚስት ነበሩ መካንነታቸውን ሰበብ አድርገው ሕገ ጋብቻቸውን ያላሰደፉ ንፁሐን ነበሩ።

አምላካችን እግዚአብሔርም ንፅሕናቸውን ቅድስናቸውን ተመልክቶ ከብዙ ደጅ ፅናት (ፆምና ፀሎት) በኋላ ልጅ እንድትሆናቸው እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሰጣቸው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ነሐሴ 7 ቀን ተፀንሳለች በተፀነሰችም ጊዜ ብዙ ተአምራት ተደርጓል።የቅድስት ሃናን ማሕፀን እየዳሰሱ ዕውራን በርተዋል ጐባጦች ቀንተዋል ብዙ በሽተኞች ተፈውሰዋል ሞቶ የነበረ ሳሚናስ የሚባል የቅድስት ሃና የአጐት ልጅ የቅድስት ሃና ጥላዋ ቢያርፍበት ከሞት ተነስቶ የፀሐይ እናቱ የምትሆን ድንግል ማርያም በሃና ማህፀን መላእክት ክብሯን ሲናገሩ መስማቱን መሰከረ በዚህ ጊዜ አይሁድ ቀንተው ኢያቄምን እና ሃናን ሊገድሏቸው በጠላትነት ሲነሱ ቅዱስ ገብርኤል ሊባኖስ ወደ ሚባል ተራራ ወስዷቸው በዚያ እመቤታችን ድንግል ማርያም ግንቦት 1 ቀን ተወልዳለች።

2.2. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ቤተ መቅደስ መግባቷ

ቅዱስ ኢያቄም እና ቅድስት ሃና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በንፅህና በቅድስና በቤታቸው 3ዓመት ካሳደጓት በኋላ ስዕለት ተሰለው ስለነበር የወለዷት “የሰጠ ቢነሳ የለበት ወቀሳ”ብለው ለቤተ እግዚአብሔር የሚያስፈልገውን እጅ መንሻ ይዘው እመቤታችንን ለቤተ እግዚአብሔር እንድታገለግል ሊሰጧት ወደ ቤተ መቅደስ አመጧት ካህኑ ዘካርያስም መጥቅዕ (ደወል) መትቶ ህዝቡን ሰበሰባቸው ሕዝቡም ሲሰበሰቡ ቀድሞ ለቤተ መቅደሱ አገልግሎት ስዕለት ይመጣ የነበረው ወርቅ፣ብር፣በሬ፣በግ፣ ነበር አሁን ግን ሰው ነው።ይህቺን ብላቴና ተቀብለን ምን እናበላታለን ምን እናጠጣታለን የት እናኖራታለን ብሎ ህዝቡን ቢጠየቃቸው ።በዚህ ነገር ሲጨነቁ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ፋኑኤልን ጎብስት ሰማያዊ ፅዋዕ ሰማያዊ አስይዞ ወደ እነርሱ ላከው ከሊቀ ካህኑ ጀምሮ ሌሎችም እንደየ ማዕረጋቸው ይህንን እንቀበላለን ብለው ሲቀርቡ ለእነርሱ ስላልመጣ ከእነርሱ እራቀ በኋላ እመቤታችንን ከሰው ለይተው ለብቻዋ ባቆሟት ጊዜ ከሰማይ ወርዶ አንድ ክንፉን አንጥፎ አንድ ክንፉን ጋርዶ እመቤቴ ደጅ ባስጠናሁሽ ይቅር በይኝ ብሎ መግቧት አርጓል።የምግቧ ነገር ከተያዘ ከሰው ጋር ምን ያጋፋታል ቤተ መቅደስ ትኑር

ብለው በታህሣስ 3 ቀን ወደ ቤተ መቅደስ አስገብተዋታል።በዚያም ህብስት ሰማያዊ ፅዋዕ ሰማያዊ እየተመገበች መላእክት እያረጓጓት ሐር እና ወርቅ እያስማማች እየፈተለች ቤተ መቅደሱን እያገለገለች 12 ዓመት ተቀምጣለች።አባ ሕርያቆስም ይህንን ሲያነላ በቅዳሴ ማርያሙ እንዲህ ብሏል "ድንግል ሆይ ምድራዊ ህብስትን የተመገብሽ አይደለሽም ከሰማየ ሰማያት የበሰለ ሰማያዊ ህብስትን እንጂ ድንግል ሆይ ምድራዊ መጠጥን የጠጣሽ አይደለሽም ከሰማየ ሰማያት የተቀዳ ሰማያዊ መጠጥን እንጅ ድንግል ሆይ ከአንቺ አስቀድሞ ከአንቺም በኋላ እንዳሉ ሴቶች እድፍ ጉድፍ የምታውቂ አይደለሽም በንፅህና በቅድስና በቤተ መቅደስ ኖርሽ እንጂ ድንግል ሆይ የሚያታልሉ ጦልማሶች ያረጋጉሽ አይደለም የሰማይ መላእክት ጦበኙሽ እንጂ።"እንዲል።

2.3. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አረጋዊ ዮሴፍ እንዲጠብቃት መሰጠቷ

ከ12 ዓመት በኋላ አይሁድ በእመቤታችን ላይ በምቀኝነት ተነስተው በእናት በአባቷ ቤት 3 ዓመት በቤተ መቅደስ 12 ዓመት በድምሩ 15 ዓመት ሆናት ልማደ አንስት ታደርሳለች ቤተ መቅደሳችንን ታሳድፋለች ትውጣ አለ ካህኑ ዘካርያስ ወደ እመቤታችን ገብቶ ነገራት እርስዋም ወደ እግዚአብሔር አመልክትልኝ እንጂ እኔ ምን አውቃለሁ አለችው እርሱም ወደ እግዚአብሔር ሲያመለክት ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን የእስራኤል ሽማግሌዎች በትራቸውን ሰብስበህ ስትፀልይበት እደር እኔ ምልክት አሳይሃለሁ አለው እርሱም እንደ ታዘዘው ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን ሽማግሌዎች በትራቸውን ወደ ቤተ መቅደስ አስገብቶ ሲፀልይ አድሮ ሲነጋ ቢያወጣው የዮሴፍ ወልደ ዳዊት በትር ሰው ሳይተክላት ውሃ ሳያጠጣት ለምልማ አብባ አፍርታ ዮሴፍ ሆይ ድንግል ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ የሚል ቃል ተፅፎበት ተገኘ ዕጣም ቢጣጣሉ ለዮሴፍ ደርሳዋለች።ርግብም በእራሱ ላይ አርፋለች በእነዚህ ሦስት ምልክቶች ዮሴፍ አረጋዊ እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን እንዲጠብቃት (እንዲያገለግላት) በመመረጡ እመቤታችን ለዮሴፍ ተሰጥታዋለች አባ ሕርያቆስም በቅዳውድንግል ሆይ ለዮሴፍ የታጨሽ ለመገናኘት አይደለም ንፁህ ሆኖ ሊጠብቅሽ ነው እንጂ እንዲል።ድንግል ማርያም ለዘመዷ ለዮሴፍ ንፁህ ሆኖ ይጠብቃት ዘንድ በአደራ ተሰጠሽ።ከርሀራሄዋ ብዛት የተነሣም በቤተ ዮሴፍ ሳለች ዮሴፍን ትረዳው (ታገለግለው) ነበርና ውሃ ስትቀዳ የተጠማ ውሻ አግኝታ በወርቅ ጫማዋ ውሃ አጠጥታዋለች።

2.4.እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ቅዱስ ገብርኤል እንዳበሰራትና ጌታን መውለዷ

ከዚህ በኋላ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መጋቢት 29 ቀን በዕለተ እሁድ በ3 ሰዓት በቤተ መቅደስ ሳለች በቅዱስ ገብርኤል አብሳሪነት አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልደው በነገራት ጊዜ እርሷም በእምነት ይሁንልኝ ባለች ጊዜ የአምላክ እናት ለመሆን ተመርጣለች::ሉቃ 1፥26-38 ጌታን በ9 ወር ከ5 ቀን በኋላ ታህሣስ 29 ቀን ምጥ ሳይሰማት የደም

መፍሰስ አራስነት ሳያገኛት በቤተልሔም ግርግም በድንግልና ወልዳዋለች ከወለደችውም በኋላ በዘለዓለማዊ ድንግልና ፀንታ ኖራለች። (ኢሳ 7፥14፣ሉቃ 2፥1-20)።

2፡5.የእመቤታችን ስደት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን በወለደችው ጊዜ ሰብአ ሰገል ኮከብ መርቶ ከሩቅ ምስራቅ (ባቢሎን) ወደ ኢየሩሳሌም አደረሳቸው ኮከቡም ኢየሩሳሌም ሲደርሱ ተሰወረባቸው እነርሱም የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት አለ? ብለው ጠየቁ በጊዜው የነበረው ንጉሥ ሄሮድስ ከሰራዊቱ ጋር ይህንን ሰምቶ ደነገጠ ካህናተ አይሁድን ጠርቶ ንጉስ የት እንደሚወለድ ጠየቀ እነርሱም ቤተልሔም እንደሆነ ነገሩት እርሱም ሰብአ ሰገልን ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ጊዜ ጠየቃቸው እነርሱም 2 ዓመት እንደሆነው ነገሩት እነርሱን ወደ ቤተልሔም እንዲሄዱ ላካቸው ኮከቡም ተገለጠላቸው ቤተልሔም ደርሰው ህፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አገኙት ሳጥናቸውን ከፍተው ወርቅ እጣን ከርቤ እጅ መንሻ አገቡለት ከዚያም የጌታ መልአክ በሌላ መንገድ በ40 ቀን ወደ ሀገራቸው አስገባቸው።።እነርሱም ከሄዱ በኋላ የጌታ መልአክ በሕልም ተገልፆ ህፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር ይዞ ወደ ግብፅ እንዲሰደድ አረጋዊ ዮሴፍን አዘዘው በዚህ ትእዛዝ መሰረት እመቤታችን ጌታን ይዛ ወደ ግብፅ ወርዳለች (ተሰድዳለች) በስደቷ ወራት ስለ ልጇ ስትል ተርባለች ተጠምታለች የእመቤታችን ስደት ለ3 ዓመት ከስድስት ወር ነበር ሄሮድስም ጌታን የሚያገኝ መስሎት በርከት ያለ ቁጥር ያላቸውን የቤተልሔም ሕፃናት በግፍ እንዲጨፈጨፉ አድርጓል።።ማቴ 2፡13-21፣ራዕ12፡12፣ኢሳ19፡1፣ሆሴ11፡1

2፡6 እመቤታችን በጌታችን የማስተማር ዘመን

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በጌታችን የማስተማር ዘመን አብራ አልተለየችም በተለይ ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በዮሐ 2፡1-11 ላይ እንደገለፀው በቃና ዘገሊላ የመጀመሪያው ተአምር ሲፈፀም ማለትም ውሃው ወደ ወይን ጠጅነት ሲቀየር ውሃው ወደ ወይን ጠጅነት ለመቀየሩ ምክንያት የእመቤታችን አማላጅነት እንደሆነ ገልፆል።።ከዚያም ጌታችን ዙሮ ካስተማረ በኋላ በመልዕልተ መስቀል ሲሰቀል ከእግረ መስቀሉ አብራ ነበረች በዚህ ጊዜ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ድንግል ማርያምን ለዮሐንስ እናት እንድትሆነው ሰጥቶታል።።ዮሐንስን ደግሞ ለድንግል ማርያም ልጅ እንዲሆናት ሰጥቷታል።። ቅዱስ ወንጌል እንደሚለው ዮሐንስ ወንጌላዊ ወደ ቤቱ ወስዷታል።።ዮሐ 19፡26 በዮሐንስ አማካኝነት እኛ የድንግል ማርያም የፀጋ ልጆች መሆናችን ድንግል ማርያም ደግሞ የፀጋ እናታችን መሆኗ በዚህ ተረጋግጧል።።

2፡7 እመቤታችን ከሐዋርያት ጋር

ወንጌላዊው ዮሐንስ አመቤታችንን ወደ ቤቱ ወሰዳት ሲባል ወደ መጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ማርቆስ እናት ቤት ወደ ማርያም ቤት አመጣት ማለት ነው፡፡ በዚያ ሐዋርያት ይሰባሰቡ ነበር፡፡ ሐዋርያትም ከጌታ ሞት እና ትንሳኤ እንዲሁም እርገት በኋላ የሚሰጣቸውን ፀጋ መንፈስ ቅዱስን ተስፋ አድርገው ድንግል እመቤታችንን ማርያምን ስበው ፀሎት ያደርጉ ነበር፡፡ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ተቀብሎ ከሞት በተነሳ በ50ኛው ቀን በክብር ባረገ በ10ኛው ቀን መንፈስ ቅዱስን ልኮላቸው 72 ቋንቋ ተግልያላቸው መከራውን ሁሉ ታግሰው ዓለምን ዙረው አስተምረዋል፡፡ አባቶቻችንም ይህንን ታሪክ መነሻ አድርገው እመቤታችንን ሲያመሰግኗት ሞገስ ስብከቱሙ ለሐዋርያት የሐዋርያት የስብከታቸው ሞገስ አንቺ ነሽ ብለው አመስግነዋታል፡፡ ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል እመቤታችንን ከበው መፀለያቸው እንደጠቀማቸው እኛም በእመቤታችን ተማፅነን በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እንድናገኝ ያስፈልጋል፡፡ ሐዋ 1፡12-14፣ ሐዋ 2፡1

2.8 የእመቤታችን እረፍት፣ትንሣኤ እና ዕርገት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታ ጋር 33 ዓመት ከ3-ወር አብራ አልተለየችም ጌታችን በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ሳለ ከእግረ መስቀሉ ሥር አብራ ነበረች።ጌታም ለሚወደው ደቀ መዝሙር ለቅዱስ ዮሐንስ አደራ ሰጣት ቅዱስ ዮሐንስም ወደ ቤቱ ወስዶ አገለገላት።(ዮሐ 19፥26)። እመቤታችንም በዮሐንስ ቤት ለ15 ዓመት ተቀምጣለች በድምሩ 64 ዓመት ሲሆናት ጥር 21 ቀን በ49 ዓ.ም ገደማ ከዚህ ዓለም ድካም አርፋለች።

በኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን እንደሚተረከው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት በሆነበት ዕለት ሐዋርያት የእመቤታችንን ሥጋ (አስክሬን) ለማሳረፍ ወደ ጌቴ ሴማኒ መካነ ዕረፍት (የመቃብር ቦታ) ይዘው ሲሄዱ አይሁድ በቅንአት መንፈስ ተነሳስተው ቀድሞ ልጇን በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ በአርባኛው ቀን ወደ ሰማይ ዐረገ እንደገናም ተመልሶ ይህን ዓለም ለማሳለፍ ይመጣል።እያሉ በማስተማር ሕዝቡን ፈፅመው ወስደውታል።አሁን ደግሞ ዝም ብለን ብንተዋት እርሷንም እንደ ልጇ ተነሣች ዐረገች እያሉ በማስተማር ሲያውኩን ሊኖሩ አይደለምን? ኑ!ተሰብሰቡና በእሳት እናቃጥላት ብለው ተማክረው መጥተው ከመካከላቸው ታውፋንያ የተባለ ጎበዝ አይሁዳዊ ተመርጦ ሄደ የእመቤታችንን ሥጋ (አስክሬን)የተሸከመበትን አልጋ ሸንኮር ያዘ የአልጋውን ሸንኮር በያዘ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ሰይፍ ሁለት እጆቹን ስለቆረጣቸው ከአልጋው ሸንኮር ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ።

ነገር ግን ታውፋኒያ በፈፀመው ድርጊት ተፀጽቶ ወደ እመቤታችን ለተማፀነ በኅቡዕ ተአምር የተቆረጡ እጆቹን እንደ ቀድሞው አድርጋ ፈውሳቸዋለች።

በዚያን ጊዜም መልአከ እግዚአብሔር የእመቤታችንን ሥጋ (አስክሬን) ከሐዋርያው ከዮሐንስ ጋር ነጥቆ ወስዶ በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አስቀመጠው ቅዱስ ዮሐንስም ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ሐዋርያት ሲመጣ የእመቤታችን ሥጋ (አስክሬን) በገነት መኖሩን ነግራቸው ሐዋርያትም የእመቤታችንን ሥጋ (አስክሬን) አግኝተው ለመቅበር በነበራቸው ምኞትና ጉጉት የተነሣ ነሐሴ 1 ቀን ሱባኤ ጀምረው ሲጸሙና ሲፀልዩ ከሰነበቱ በኋላ በ14ኛው ቀን (በሁለተኛው ሱባኤ መጨረሻ)ጌታችን የእመቤታችንን ትኩስ ሥጋ አስክሬን አምጥቶ ስለሰጣቸው በታላቅ ዝማሬ በውዳሴና በጽኑ ምሕላ ወስደው ቀድሞ በተዘጋጀ መካነ ዕረፍት በጌቴ ሴማኒ ቀበሯት።

የእመቤታችን የቀብር ሥነ ሥርዓት በተፈጸመ ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነው ቅዱስ ቶማስ አልነበረምና ከሀገረ ስብከቱ ከህንድ በደመና ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ እመቤታችን በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ ትንሣኤ ተነስታ ስታርግ ያገኛታል። በዚያ ጊዜም ትንሣኤዋን ሌሎቹ ሐዋርያት አይተው ለእርሱ የቀረበት መስሎት ተበሳጭቶ ፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ ይለዋል ማለትም በፊት የልጅሽን ትንሣኤ አሁን ደግሞ የአንቺን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ ብሎ ከማዘኑ የተነሣ ከደመናው ተወርውሮ ሊወድቅ ቃጣው በዚህ ጊዜ እመቤታችን ከእርሱ በቀር ሌሎች ሐዋርያት ትንሣኤዋን እንዳላዩ ነግራው ቅዱስ ቶማስን አፅናናችው ሄዶም ለወንድሞቹ ለሐዋያት የሆነውን ሁሉ እንዲነግራቸው አዘዘችው ለምልክት ምስክር ይሆነው ዘንድ የተገነዘችበትን ሰበኗን ሰጥታው በመላእክት ታጅባ እየተመሰገነች ወደ ሰማይ ዐርጋለች።

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስም ሐዋርያት ወደ አለበት ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ እመቤታችንን እኮ ቀበርናት ብለው ነገሩት እርሱም ዐውቆ ምስጢሩን ደብቆ አይደረግም ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር እንደምን ይሆናል አላቸው።አንተ እንጅ ቀድሞ የጌታን ትንሣኤ ተጠራጠርክ አሁንም አታምንምን ብለው በቅዱስ ጴጥሮስ መሪነት ወደ እመቤታችን መካነ መቃብር ይዘውት ሄደው ሊያሳዩት መቃብር ቢከፍቱ የእመቤታችንን ሥጋ አስክሬን አጡት ደነገጡም በዚህ ጊዜም ቅዱስ ቶማስ አታምኑኝም ብዬ ነው እንጂ እመቤታችንስ ተነሥታ ዐርጋለች ብሎ የሆነውን ሁሉ ከተረከላቸው በኋላ ለማረጋገጫ ምልክት እንዲሆን የሰጠችውን ሰበኗን አሳየችው እነርሱም ሰበኗን ቆራርጠው ከተከፋፈሉት በኋላ ወደ አህጉረ ስብከታቸው ሄደዋል።

በዓመቱ ትንሣኤሽን ቶማስ አይቶ እኛ እንዴት ይቅርብን ብለው ከነሐሴ 1 ቀን ጀምሮ ሱባኤ ገቡ በሱባኤው መጨረሻም በነሐሴ በአሥራ ስድስተኛው ቀን (ነሐሴ 16) ቀን ጌታችን የለመኑትን ልመና ተቀብሎ እመቤታችንን መንበር፣ቅዱስ ጴጥሮስን ንፍቅ (ረዳት) ቄስ፣ቅዱስ እስጢፋኖስን ገባሬ ሰናይ ዋና ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ ሁሉንም ከአቆረባቸው በኋላ የእመቤታችንን ዕርገቷን

ለማየት አብቅቷቸዋል።የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ትንሳኤ እና ዕርገት በትንቢተ ነቢያት የተነገረ ነበር።(መዝ 131፥8፣መኃ 2፥10-15)።

2.9 ስመ ድንግል ማርያም

በእስራኤላውያን ዘንድ "ስም" ጠባይን፣ግብርንና ሁኔታን እንደሚገልጥ ሁኖ ይሰየማል። ከዚህ የተነሳ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም እናት እና አባት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም "ማርያም" ብለው አወጡላት ይህ ስም የእመቤታችንን ማንነት የሚገልጥ ነው።ለመሆኑ "ማርያም" ማለት ምን ማለት ነው?

- **ማርያም ማለት**፦ በእብራይስጥ ማሪሃም ማለት ሲሆን እመ ብዙኃን የብዙዎች እናት ማለት ነው።አብርሃም ማለት አበ ባዙኅን (የብዙዎች አባት) ማለት እንደሆነ ዘፍ 17፥5

- **ማርያም ማለት**፦ መርሕ ለመንግስተ ሰማያት ወደ መንግስተ ሰማያት መርታ የምታስገባ ማለት ነው።ምክንያቱም ከሕገ እግዚአብሔር የወጣው ከፀጋ እግዚአብሔር የተራቆተው አዳም ወደ ቀደመ ክብሩ እንዲመለስ ምክንያት ድህነት የሆነችው ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ናትና ወደ መንግስተ ሰማይ መርታ የምታስገባ ትባላለች።

የእመቤታችን አማጅነት ተስፋ ሳያደርግ ወደ መንግስተ ሰማይ መግባት የሚቻለው የለምና።

- **ማርያም ማለት**፦ ፀጋ ወሃብት ማለት ነው ለጊዜው እናትናአባቷ በሰው ዘንድ ባለ ልጅ መውለዳቸው ተንቀው ተዋርደው ይኖሩ ነበር እርሷን በመውለዳቸው ተከብረውባታል ስለዚህ ለእናትና ለአባቷ ፀጋ እና ሃብት ሁና ተሰጥታለች።

ለፍፃሜው አማላጅነቷን አውቀው ቃል ኪዳኗን አምነው ለሚመጡ ምዕመናን ሁሉ በዮሐንስ ወንጌላዊ አማካኝነት ለምዕመናን ሁሉ እናት አማላጅ ሁና ተሰጥታለች።ስለዚህ ማርያም ተብላለች። (ዮሐ 19፥26፣ሉቃ 1፥28-30)።

- **ማርያም ማለት**፦ ፍፅምተ ሥጋ ወነፍስ ማለት ነው።ፍፅምት ማለት ምንም አይነት እንከንና ጉድለት የሌለባት ንፅሕተ ንፁሐን ቅድስተ ቅዱሳን አዳማዊ በደል (ጥንተ አብሶ) ያልነካት ማህደረ እግዚአብሔር ትሆን ዘንድ የተገባት ማለት ነው። እንኳን እመቤታችን በፀጋ ያከበራቸው ቅዱሳንም ከፍፁምነት መድረሳቸውን መፃህፍት ምስክር ሆነዋል።(ዘፍ 6፥1፣ኢዮብ 1፥1)።

- ***ማርያም ማለት***፦መልዕልተ ፍጡራን ከፍጡራን በላይ ስንል ከ 22 ሥነ ፍጥረት ማለታችን ነው።ከእነዚህም ፍጡራን መካከል እግዚአብሔር አክብሮና አልቆ የፈጠራቸው ሰውንና

መላእክትን ነው ሰውና መላእክት በተለየ ክብር መፈጠራቸው ዛሬ ሕጉን አክብረው ስሙን ቀድሰው በኋላ ክብሩን ስለሚወርሱ ነው።እመቤታችን ከፍጡራን በላይ ናት ስንልም ከሰው ልጆችም ሆነ ከመላእክት የምትከበር ማለታችን ነው።ምክንያቱም በቅዱሳን መላእክትም ሆነ በቅዱሳን አባቶቻችን እግዚአብሔር በረድኤት አድሮባቸው ይኖራል።እመቤታችን ድንግል ማርያም ግን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ በፍፁም ተዋህዶ ዓለምን ለማዳን ምሕረቱን የገለጠባት እመ መሐሪ በመሆኗ ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ ከእርሷ በቀር ማንም የለም።

ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ "የዐቢ ክብራ ለማርያም እምኩሎሙ ቅዱሳን" የማርያም ክብር ከቅዱሳን ክብር ይበልጣል።ይህች ከኪሩቤል ትበልጣለች.....ከሱራፌልም ትበልጣለች ከሦስቱ አካል ለአንዱ (ለእግዚአብሔር ወልድ) ማደሪያ ሆናለችና ብሏል።

- **<u>ማርያም ማለት</u>**፦ ተላኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው።አካላዊ ቃል በእመቤታችን አድሮ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፈስዋ ነፍስ ነስቶ መለኮትን ከትስብእት (ከሥጋ) ትስብእትን ከመለኮት አዋሕዶ ፍፁም አምላክ ፍፁም ሰው ሆኖ ስለተገለጠባት ለአምላክ ሰው የመሆኑ ምክንያት ለሰው የመዳኑ ምክንያት ናትና "ተላኪተ እግዚአብሔር ወሰብዕ" ትባላለች።የሰውን ልመና ወደ እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ይቅርታ ወደ ሰው በማድረስ ወደ ሰው በማድረስ ድህነተ ሥጋ ድህነተ ነፈስ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እያማለደች ታሰጠናለችና።ተላኪተ እግዚአብሔር ወሰብዕ ተብላለች።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ሥሞች እንዳሉ ሆነው ሌላ ምስጢራዊ ወይም ዘይቤያዊ ስሞችም አሏት እነርሱም፦

<u>ሀ.እመ ብርሃን</u>፦ የብርሃን እናት ማለት ነው።ጌታችን እና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው (በማስተማር ዘመኑ) እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ።ብሏል (ዮሐ 8፥12) ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በራዕዩ ሴት ብርሃን ተጎናጽፋ ጨረቃ ተጫምታ 12 ከዋክብት የተቀረፀበት ዘውድ ደፍታ ተገለፀችልኝ ብሏል።(ራዕ 12፥1)።

ብርሃን የተባለ የባሕርይ አምላክ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ የእርሱ እናት ደግሞ ድንግል ማርያም ስለሆነች ይህ እመ ብርሐን የተሰኘው ስም ይገባታል።

<u>ለ.ወላዲተ አምላክ</u>፦ የአምላክ እናት ይህ ስም ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የሚገባት ነው።ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ የሆነ በተዋሕዶ የከበረ የወልደ እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እናት ለመሆን ከሴቶች መካከል የተመረጠች እርሷ

በመሆኗ ነቢዩ ኢሳይያስም በትንቢቱ እንደተናገረው ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ድንቅ መካር ኃያል አምላክ ነው።(ኢሳ 9፥6)። በሌላም ሥፍራ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የምትወልደው አምላክ ስሙ አማኑኤል ተብሎ እንደሚጠራ ተናግሯል።(ኢሳ 7፥14)። "አማኑኤል" ማለትም የእግዚአብሔር መልአክ እንደተረጐመው እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነሥቶ ሰው ሆነ ማለት ነው።(ማቴ 1፥23)።

በብሉይ ኪዳን ነቢያት "ይቤ እግዚአብሔር" እያሉ የተናገሩት ትንቢቱ በኢየሱስ ክርስቶስ መፈፀሙ የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት የባህርይ አምላክ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው። (ኢዮ 2፥32፣የሐዋ ሥራ 2፥21-38፣ሮሜ 10፥9-13፣ኢሳ 40፥3፣ማር 1፥1-3)።እነዚህን ብቻ ማመሳከሩ በቂ ነው።ይህንን ሁሉ ይዘን ድንግል ማርያም ለአምላክ እናትነት ብቻ የተፈጠረች የእግዚአብሔር እናት ናት እንላለን።ከዚህ የወጣ ትምህርት የለም ቢኖርም የመናፍቃን ትምህርት ነውና ተቀባይነት የለውም።

በተጨማሪም የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት አባታችን ቅዱስ ቄርሎስ "አማኑኤልየባሕርይ አምላክ እንደሆነ ንጽሕት ድንግልም አምላክን የወለደች እንደሆነች ሰው የሆነ የእግዚአብሔርንም ቃል እንደወለደች የማያምን ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን" በማለት ከአወገዘ በኋላ "ዳግመኛ በኋላ ዘመን ቅድስት ድንግል እርሱን በሥጋ በወለደችው ስለእኛ ሰው የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ወለደችው።"ስለዚህም ቅድስት ድንግልን ወላዲተ አምላክ እንላታለን።ሰው ሳይሆን ሰውም ከሆነ በኋላ አንድ ወልድ አንድ ክርስቶስ ነው።ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ቃል ሌላ አይደለም ከቅድስት ድንግል የተወለደውም ሌላ አይደለም የምናምንበት ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ከድንግል በሥጋ የተወለደ ይህ አንድ ወልድ ነው እንጂ (ሃ.አ.ገጽ 277-305) በማለት ቅድስት ድንግል ማርያም እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ መሆኗን መስክሯል።

ሐ.<u>ኪዳነ ምሕረት</u>፦ ኪዳን ውል ስምምነት መሓላ የሚል ትርጉም ሲኖረው ምሕረት፣ቸርነት፣ ነፃ ስጦታ፣ፍቅርን የሚያመለክት ሀይለ ቃል ሲሆን ይህ ስም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታችን ከአምላካችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስምሽን የጠራ እምርልሻለሁ የሚል ስለ ሓጥአን የተሰጣትን የምሕረት ቃል ኪዳን ማሳሰቢያ ነው።(መዝ 88፥3) "ከመረጥኳቸው ጋር የምሕረት ቃል ኪዳንን አደረግሁ።"እንዲል።

<u>ማጠቃለያ</u>

በዚህ ምዕራፍ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ታሪክ የትውልድ ሐረግ የእመቤታችን ልደት እና አስተዳደግ እንዲሁም ስሞቿ የተገለፁ ሲሆን በይበልጥ ተማሪዎች ከዚህ በፊት ስለ እመቤታችን ታሪክ የሚያውትን አዲስ ከተማሩት ጋር በማገናዘብ ለእመቤታችን የበለጠ ክብር

እንዲሰጡ እና ታሪክ ድንግል ማርያምን የበለጠ አውቀው በህይወታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማሳየት ተሞክል፡፡በይበልጥ መምህራን በመጠየቅ እና በዚህ ዙሪያ የተፃፉ ሌሎች መፃህፍትን በማንበብ የበለጠ ትምህርቱን ሊያዳብሩት ይገባል፡፡

ዋቢ መጻሕፍት

1. ወንጌል አንድምታ
2. ውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ
3. ወላዲተ አምላክ በመፅሐፍ ቅዱስ
4. ነገረ ማርያም በማኅበረ ቅዱሳን

ምዕራፍ ሦስት

ነገረ ማርያም በነገረ ድኅነት

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ያላትን ሱታፌ ማለትም አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ባደረገው ሥራ ውስጥ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከእናትነት እስከ መስቀል ድረስ ያደረገችውን አገልግሎት በስፋት የምንመለከትበት ሲሆን በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ለአዳም የገባውን ቃል ኪዳን በእመቤታችን እንደፈፀመለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጥንተ አብሶ (ስውር ሃጢአት) የተለየች የነፃች መሆኗን እና ስለ ንፅሕናዋ ስለ ቅድስናዋ ስለ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋ ድንግልናዋ የምንመለከትበት ሲሆን የእመቤታችን ምልጃ በነገረ ድህነት ለሰዎች ያለውን ጥቅም የበለጠ የምንመለከትበት ይሆናል፡፡

በዚህ ዓቢይ ርዕስ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በሰው ልጆች መዳን ያላትን ሱታፌ (ድርሻ) የምንመለከትበት ነው።

ጥያቄ

ሀ.እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድህነት(በሰው መዳን) ያላትን ሱታፌ አብራራ

ለ.ጥንተ አብሶ ማለት ምን ማለት ነው

ሐ.የእመቤታችን ምልጃ በነገረ ድህነት ውስጥ እንዴት እንደሆነ ግለፅ፡፡

ነገረ ማርያም በነገረ ድኅነት

“ነገረ ድኅነት” ስንል በሀጢአት ምክንያት የወደቀውና የጎሰቆለው የሰው ልጅ ከደረሰበት ድቀትና ሞት ሙሉ በሙሉ ነፃ መውጣቱንና አጥቶት የነበረውን ፀጋ ማግኘቱን ማለትም ተፈርዶበት በነበረው የሞት ፍርድ የተወገደለት መሆኑን ከሞት ወደ ህይወት ከመገዛት ወደ ነፃነት ከባርነት ወደ ልጅነት ከሲኦል ወደ ገነት መሸጋገሩን መናገር ነው፡፡ ይኸውም አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሳው ሥጋ በፈፀመልን ፍፁም ካሣ ነው፡፡ስለዚህ በሰው ድህነት ትልቁን ድርሻ ይዛ የምትገኝ የእመቤታችን ነገር በዚህ ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡ አበው “ነገር ከሥሩ ውሃ ከጥሩ” እንዲሉ ከኪዳነ አዳም እንጀምራለን፡፡

3.1.ኪዳነ አዳም

አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሥነ-ፍጥረትን “እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ” (ካለመኖር ወደ መኖር) አምጥቶ በቸርነቱ ሲፈጥራቸው የፍጥረት ሁሉ ቁንጮ “ሰው” (አዳም) ነው።ምክንያቱም በመልኩ በአርአያው በምሳሌው ፈጥሮታልና ከፈጠረው በኋላም ሕግ ሰርቶለታል ይህችውም የመታዘዝ ሕግ የመጠበቅ ምልክት ዕፀ በለስን እንዳይበላ መጠበቅ ነው።

ይህንን ህግ ለ7 ዓመት ከ3 ወር ከ10 ቀን ጠብቆ ከኖረ በኋላ በምክረ ከይሲ በዲያብሎስ ምክር ተታሎ አምላክነት ሽቶ (ተመኝቶ) ዕፀ በለስን በበላ ጊዜ “ኮናኔ በርትዕ ፈታሔ በጽድቅ” የሆነ እግዚአብሔር አምላክም የምትሞት ትሞታለህ ብሎ እንደነገረው ፍርዱንም ፈረደበት ከገነትም አባረረው አባታችን አዳምም ከገነት ከወጣ በኋላ እግዚአብሔርን ፍፁም እንደበደለው አውቆ ንስሐ ገባ የስንዴ ፍሬም ከደሙ ጋር ቀላቅሎ ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጐ አቀረበ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔርም የአሁኑን ተቀብዬልሃለሁ ዓለም የሚድነው በአንተ ደም ሳይሆን በእኔ ልጅ ደም ነው አምስት ቀን ተኩል ሲፈፀም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በሚዳህ ድሃ በመስቀል ሞት አድንህለሁ ብሎታል።

በዚህ የአዳም ቃል ኪዳን ልጅህ የተባለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እም ገነት ትርጉም ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ ብሏታል አምስት ቀን ተኩልም የተባለው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ነው ይህ እንደተፈፀመም ቅዱስ ጳውሎስ ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏል ነገር ግን የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ።(ገላ 4፥4 ቅ.ጳውሎስ)።

- የዘመን ፍፃሜ ብሎ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመንን
- ሴት ብሎ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን
- ልጅ ብሎ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን አነሳ።

3.2.ጥንተ አብሶ

ጥንተ አብሶ ማለት የውርስ ሐጢአት ማለት ነው ይህም ከአዳም መረገም የተነሳ በሰው ልጆች ከአንዱ ወደ አንዱ በዘር የሚወረስ ቁራኝነት ነው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን ከዚህ ሁሉ ማለት በዘር ከሚሆነው ሀጢአት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጠብቋታል መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እም ከርሰእማ እንዲል ይህንንም ነቢዩ ኢሳይያስ ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏል ት.ኢሳ 1፥9። እግዚአብሔር ፀባኦት እመ ኢያትረፈ ለነ ዘርዐ ከመ ሰዶም እም ኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ <u>ትርጉም</u>፡- አሸናፊ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን ነበር በማለት እንደተናገረ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአምላክ ጥበብ ከእናቷ ማሕፀን ጀምራ በአዳም በደል ከመጣው ከመርገመ ሥጋ እና ከመርገመ ነፍስ ተጠብቃ ያለች ንጽህት ዘር መሆኗን ትንቢት ተናግሮለታል።

ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት በእመቤታችን የተፈፀመ ማለትም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፈስ የሌለበት መሆኑን ቅዱስ ገብርኤልም ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ መጥቶ መስክሯል።ተፈስሒ ፍስሕት ኦ ምልዕተ ፀጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ትርጉም ፀጋን የተመላሽ ደስተኛይቱ ሆይ ደስ ይበልሽ ጌታ ካንቺ ጋር ነው ቡርክት አንቲ አንስት አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ።ሉቃ 1፥28።በማለት መልአኩ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

ይህንን የነቢዩ የኢሳይያስንና የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ምስክርነት በመያዝ በርካቶች ቅዱሳን አባቶችም ቅድስት ድንግል ማርያም በአምላካዊ ጥበብ ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ (በጥንተ አብሶ) ተጠብቃ የኖረች ንጽህት ዘር ስለ መሆኗ በስፋት መስክረዋል ከሊቃውንቱ መካከል ማህቶተ ቤተ ክርስቲያን የተባለው ቅዱስ ያሬድም በድጓ ድርሰቱ እንዲህ ብሏል “ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሡ ለአዳም ከመባሕርይ ፀዐዳ”ትርጉም ማርያምስ ከጥንት ጀምሮ በአዳም ባሕርይ ውስጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች ማለት ነው ድጓ ገጽ 379 ይህ ማለት ዕንቁባሕርይ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች አዲስ መዝገብ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም አዳም አትብላ የተባለውን ዕፀ በለስን በመብላቱ ምክንያት ከመጣበት የሥጋና የነፍስ መርገም በጌታ ጥበብ ተጠብቃ የኖረች መሆኑን ሲገልጥ እንደ ነጭ ዕንቁ ታበራለች ብሏል።

ምሥጢሩ ይህቺን ነጭ ዕንቁ ከደፈረሰ ባሕር ውስጥ ቢጥሏት እንኳን የደፈረሰው ባሕር የርሷን ጥራት ሳይለውጠው በደፈረሰው ባሕር ውስጥ ሳለች አበርታ እንደምትታይ ሁሉ ልክ እንደ ዕንቁዋ ቅድስት ድንግል እመቤታችን ማርያምም በአዳም ትዕዛዝ መተላለፍ ከመጣ መርገመ ሥጋ

መርገመ ነፍስ በአምላካዊ ጥበብ ተጠብቃ በንፅሕናና በቅድስና ፀንታ የተገኘች መሆኗን ሊቁ ቅዱስ ያሬድ በሚገባ ገልያታል።

መኃ.4፥7 ወዳጄ ሆይ ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም

ጠቢቡ ሰሎሞንም መንፈስ ቅዱስ የእመቤታችን ነገር እንደገለጠለት ሁለንተናሽ ውብ ነው ነውርም የለብሽም ብሎ ተናገረ ለጊዜው መልክ ከደም ግባት ጋር አስተባብራ በመገኘቷ ይህ ተነግሮላታል ለፍፃሜው ግን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ጥንተ አብሶ የሌለባት ንፅህት መሆኗን የሚያስረዳ ኃይለ ቃል ነው።

3.3.እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም

ከጌታ ጽንሰት እስከ ቀራኒዮ ያደረገችው አገልግሎት

⟶እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር ተመርጣ እናት እንደምትሆነው በነቢያት በተነገረው ትንቢት መሰረት አምላክ ዓለሙን ለማዳን የቀጠሮው ጊዜ ሲደርስ ቅዱስ ገብርኤልን ወደ እመቤታችን ላከው እርሷም ሀርና ወርቅ እያስማማች ስትፈትል ልብሱን እየታጠቀ እየፈታ ለእርሷ የሚገባውን ክብር ሰጥቶ እያመሰገናት ለእግዚአብሔር እናት እንድትሆነው መመረጧን ነገራት እርሷም እኔ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? ብላ ጠየቀችው እርሱም "ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም" አላት እመቤታችንም እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ (ገረድ) ነኝ እንደ ቃልህ ይደረግልኝ አለችው።በዚህ ጊዜ አካላዊ ቃል ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሳይለይ በተለየ አካሉ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ የዕለት ፅንስ ሆኗል።ሉቃ 1፥26።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አገልግሎት ከዚህ ይጀምራል።እግዚአብሔር ዓለሙን ለማዳን በወደደ ጊዜ እሺ ብላ እመቤታችን ፈቃደኛ በመሆኗ ከእርሷ ሰው ሆኗልና አባቶቻችን በነገረ ማርያም እንደሚያስተምሩት እመቤታችን በቤተ መቅደስ ሳለች መጽሐፈ ኢሳይያስ ስትመለከት ከትንቢተ ኢሳይያስ ም 7፥14 ላይ ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል።የሚለውን ስታነብ ከዚች ድንግል ከዘመኗ ደርሼ እንጨት ሰብሬላት ውሃ ቀድቼለት ገረድ ሆኜ ባገለገልኳት ብላ ተመኝታ ነበር አምላካችን ልዑል እግዚአብሔርም ትህትናዋን ተመልክቶ ለበለጠው አገልግሎት ለእናትነት መረጣት እርሷም በህቱም ድንግልና ፀንሳው በህቱም ድንግልና ወልዳዋለች።

ጌታችን በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል ለጌታችን የሚሆነውን እጅ መንሻ ይዘው ከሩቅ ምሥራቅ መምጣታቸውን ተመልክቶ በዘመኑ የነበረው ንጉሥ ሄሮድስ ጌታችንን ሊገድለው በምቀኝነት

ተነሳበት በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ለአረጋዊ ዮሴፍ በህልም ተገልፆ ህፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ ግብፅ እንዲሰደድ አዘዘው ከእግዚአብሔር እንደታዘዘ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ህፃን ልጇን መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስን ይዛ ለ 3 ዓመት ከ6 ወር በግብፅ በርሃ ተንከራታለች።በዚህ የመከራ ዘመንም ስለ ልጇ ስትል ተርባለች ተጠምታለች ሸፍቶች አስደንግጠዋታል የተለያዩ ብዙ መከራዎችን ተቀብላለች።እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ወቅት አገልግሎቷ መከራ በመቀበል ነበር ቅዱስ ወንጌል ምስክር እንደሆነ ማቴ 2፥13-19፣ራዕ 12፥1 ከዚያም ሄሮድስ ከነ ክፋቱ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለአረጋዊ ዮሴፍ በህልም ተገልፆ የሕፃኑን ነፍስ የሚሹት ሞተዋልና "ህፃኑን እና እናቱን ይዘህ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለስ" ብሎ አዘዘው እነርሱም፥ ማለትም እመቤታችን ጌታችን ዮሴፍ እና ሰሎሜ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰዋል።በኢየሩሳሌም ናዝሬት በተባለ ቦታ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን በዚያ አሳድጋዋለች።ማቴ 2፥22-23፣ሉቃ 2፥51-52 ሊቁ ቅ አትናቴዎስ በሃይማተ አበው ይህንን ነገር አጉልቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል ድንግል ወንድ ሳታውቅ ሊዋሀደው በፈጠረው ሥጋ የፀነሰችውን ወለደች ያለ ሀጢአት ያለ ምጥ ወለደችው የአራስነት ግብር አላገኛትም ያለ ድካም ያለ መታከት አሳደገችው ያለ ድካም አጠገባቸው ለሥጋ በሚገባ ሕግ ምን አበላው ምን አለብሰው ሳትል አሳደገችው ሃ.አበው ገፅ 86፥19።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በማስተማር ዘመኑም ከጌታችን አልተለየችም በቅዱስ ወንጌል "የመጀመሪያው ተአምር" ተብሎም የተመዘገበው ተአምር የተከወነው በእመቤታችን ምልጃ ነው።ይኸውም የውሃው ወደ ወይንነት መለወጥ ነው።ዮሐ 2፥1-11። በስተመጨረሻም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለድህነተ ዓለም በመልዕልተ መስቀል በተሰቀለ ጊዜ ከመስቀሉ ስር ነበረች ልብን በሚያቃጥል እንባ እያለቀሰች ታዝን ነበር ከእርሷ ጋር እነ ሰሎሜ እነ ማርያም መግደላዊት ሌሎችም ሴቶች ከደቀ መዛሙርቱም ቅ.ዮሐንስ ወንጌላዊ ቁመው አብረው ያለቅሱ ነበር ጌታችንም ለድንግል ማርያም ዮሐንስን እነሆ ልጅሽ አላት ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስን ደግሞ ድንግል ማርያምን "እናትህ እነኋት" አለው።ደቀ መዝሙሩ ዮሐንስ ወደ ቤቱ ወሰዳት።ዮሐ 19፥26።ይህ እንዲህ ለጊዜው በዮሐንስ አማካኝነት እመቤታችን ለሐዋርያት በእናትነት መሰጠቷን እርሷም እነርሱን በፀጋ ልጅነት መቀበሏን ያሳያል።ለፍጻሜው ግን እኛን ሁላችንን በፀጋ ልጅነት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም መሰጠቱን እና ለእኛ ለሁላችን ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በፀጋ እናት አማላጅ አድርጎ መስጠቱን የሚያመለክት ሓይለ ቃል ነው።

ሐዋርያትም ከጌታችን ሞት እና ትንሣኤ እንዲሁም በ40ኛው ቀን ማረግ በኋላ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋውን እንደሰሙ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በማርቆስ

እናት ቤት ዘግተው ደጅ ሲፀኑ (ሲፀልዩ) በመካከላቸው እመቤታችን አብራ እንደነበረች ቅ.ሉቃስ በግብረ ሐዋርያት መፅሐፍ ምስክር ሁኗል ። ዮሐ ሥራ 1፥14።

“እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለፀሎት ይተጉ ነበር” እንዲል።ሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ሊሰብኩት በየአህጉረ ስብከታቸው ሲፋጠኑ እመቤታችን አልተለየቻቸውም ነበር።ሊቁአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በሰዓታት ድርሰቱ“ሞገሰ ስብከቶሙ ለሐዋርያት” ብሏታል።ትርጉም የሐዋርያት የስብከታቸው ሞገስ አንቺ ነሽ ማለት ነው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን አገልግሎት ለመግቢያ ያህል ጠቀስን እንጅ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አገልግሎት ከነቢያት ከሐዋርያት ከቅዱሳን ሁሉ የበለጠ በፍፁም እምነት ከእናንት ፍቅር ጋር ልዑል እግዚአብሔርን ያገለገለች እናት ናት።

3.4. <u>የእመቤችን ምልጃ በነገረ ድኅነት</u>

“ድኅነት” ስንል በሀጢአት ምክንያት የወደቀውና የጎሰቆለው የሰው ልጅ ከደረሰበት ድቀትና ሞት ሙሉ በሙሉ ነፃ መውጣቱን እና አጥቶት የነበረውን ፀጋ ማግኘቱን መጀመሪያ ከመበደሉ በፊት ወደ ነበረበት ሀኔታ (ከዚያም ወደ በለጠ ደረጃ) መመለሱን ማለታችን ነው። “የሰው ልጅ ዳነ” ስንል ተፈርዶበት የነበረው የሞት ፍርድ ተወገደለት ተነስቶት (ተወስዶበት) የነበረው ሕይወት ተመለሰለት ማለታችን ነው።ይህ ድኅነት የተፈፀመው አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ፈቅዶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በህቱም ድንግልና ተፀንሶ በህቱም ድንግልና ተወለዶ በ30 ዘመኑ ተጠምቆ ዙሮ አስተምሮ በፅፀ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሞቶ ተቀብሮ በ3ኛው ቀን ተነስቶ በክብር አርጐ ደግሞ ሰው ፍፁም ካሳ ከተደረገለት በኋላ የድህነቱ ማረጋገጫ የሚሆን ጥምቀትን ቁርባንን ሥጋ ወደሙን ቤተ ክርስቲያንን ሰጥቷል።

ይህ ሁሉ ግን ለሰው የተደረገለት ከሰው በጎ ሥራ የተነሣ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል “እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንን ፈቃድ እያደረግን በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎችም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ፀጋ ስለሆነ ከወደደን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙት እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን <u>በፀጋ ድናችኋልና</u>።”ኤፍ 2፥3-8 እንዲል በሊላም ሥፍራ “ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደድ በተገለጠ ጊዜ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው ጥምቀትና በመንፈስ ቅዱስ ኪዳንን እንጂ እኛ ስላደረግነው በጽድቅ ስለነበረው ሥራ አይደለም።ቲቶ 3፥3-5 ብሏል።

ከዚህ ሁሉ ጋር ሰው በምግባር ጉድለት ቢገኝበት የመዳን ምክንያት እንዲሆንለት ቅዱሳንን በቃል ኪዳን አክብሮ ሰዎችን እንዲያማልዱ ፈቃዱ ሆኗል።ማቴ 10÷41"ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ፃድቅንም በፃድቅ ስም የሚቀበል የፃድቁን ዋጋ ይወስዳል።"እንዲል ከቅዱሳን ሁሉ የበለጠ ክብር ያላት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የተሰጣት ቃል ኪዳን እና ምልጃም አንዱ ነው ይህም የመዳን ምክንያት ነው።

<u>የእመቤታችን የቅድስት ድንግል</u>

<u>ማርያም ምልጃ</u>

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ወፍ ዘራሽ ብቅ ያለ አይደለም።ትንቢት የተነገረለት ምሳሌ የተመሰለለት በሐዲስ ኪዳን አማናዊ ሁኖ የተገለጠ ነው።

<u>ምሳሌ</u> <u>ዘፍ.7</u> "በጥፋት ውሃ ዘመን ኖህ እና ቤተሰቦቹ እንዲሁም እንስሳቱ እና አራዊቱ በመርከብ ውስጥ ሆነው ከጥፋት ውሃ ድነዋል ከመርከቡ ውጭ የነበሩ ፍጥረታት ግን ተደምስሰዋል።ይህም ምሳሌ ነው በመርከቡ ውስጥ የነበሩ የዳኑ ነፍሳት የእመቤታችን አማላጅነት ቃል ኪዳን አምነው የዳኑ የሚድኑ ነፍሳት ከመርከቡ ውጭ ሁነው (የጠፉ) በእመቤታችን ምልጃ የማያምኑ የሚጠፉ (የጠፉ) የመናፍቃን ምሳሌ የጥፋት ውሃ የሲኦል ምሳሌ ነው።

- የእመቤታችን ምልጃ በዚህ ምሳሌ እንደተገለፀ ልብ ይሏል።

ትንቢት <u>መዝ 44÷9</u> "በወርቅ ልብስ ተጐናፅፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች"

- ንግሥቲቱ ወላዲተ አምላክ በንፅሕና በቅድስና አኒጣ አንተ በሰጠሀት ክብር በወልደ እግዚአብሔር ቀኝ (ሥልጣን) የኃጥአን አማላጅ ሆና ለጥብቅና እንደምትቆም የሚያስረዳ የትንቢት ሀይለ ቃል ነው።

እንግዲህ ከላይ ለማየት እንደሞከርነው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት በምሳሌ እና በትንቢት የተነገረ ነው።አማላጅነትን በአጠቃላይ ስንመለከት ትርጓሜው የሚለምን፣ የሚፀልይ፣አማላጅ የሚሆን ማለት ሲሆን በሁለት ወገኖች መካከል በመግባት አንዱን ስለሌላው የሚማልድ ማለት ነው።በመንፈሳዊ መንገድ ስንመለከተው ደግሞ የሚለመነው ልዑል እግዚአብሔር ሲሆን የሚያማልዱት በእግዚአብሔር የተጠሩና የተመረጡ ቅዱሳን ሁሉ ይልቁንም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት።ምልጃ የታዘዘውና የተፈቀደው ያስፈለገው እግዚአብሔር ከኃጢአን ይልቅ የጻድቃንን የእመቤታችንን ፀሎት የበለጠ ስለሚሰማ ነው።መዝ 33÷15።የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ፃድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸው። እንዲል

አማላጅነት የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ ነው።ምክንያቱም ምግባራቸው የደከመና ፀሎታቸው እንደርሱ ፈቃድ ያልሆነ ተነሳሕያን ኃጥአን የእርሱን ፈቃድ በሚያውቁና በሚፈጽሙ በምግባር በበለፀጉ ፃድቃን እንዲረዱ ማድረግ የቸርነቱ መግለጫ ነው።ዘፍ 20፥1-7።"ነቢይ ነውና ስለ እናንተ ይፀልያል" ትድናለህም።እንዲል አቤሜሌክ ንጉሥ ጌራራ በፈፀመው ስሕተት እግዚአብሔርን በማስቀየሙ ይቅርታ ያገኝ ዘንድ የተላከው ወደ ቅዱሱ አብርሃም ነው።ለቅዱሳን አባቶቻችን ይህን ያህል አማልዶ ማስታረቅ ሥልጣን ከተሰጠ ለወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም እማ እንዴት የበለጠ ሀብተ ምልጃ አይሰጣት ምክንያቱም ምልዕተ ፀጋ ናትና።<u>ሉቃ 1፥28</u>።

እመቤታችን የእናትነት ክብርና የአማላጅነት ቃል ኪዳን ከልጅዋ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለች በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ልጅዋ መድኃኔዓለም ክርስቶስ ወኃውን ወደ ወይን ለውጠ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገ ው።በእመቤታችን አማላጅነት መሆኑ የታመነ ነው።<u>ዮሐ 2፥1-11</u>።እናት ወልዳ ማስገኘት ብቻ ሳይሆን ልጇን የማዘዝ መብትም አላት። በተለይ ወላዲተ አምላክ (የአምላክ እናት) የመሆኗ ትልቁ ምስጢርም የማዳን ሥራው ተካፋይ መሆን ነውና ከዚህ የተነሳ አባቶች በብሒላቸው "የእናት አማላጅ ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ ሲሆን በውድ ያለበለዚያ በግድ"። ይላሉ።ስለዚህ በእመቤታችን ቃል ኪዳን እና አማላጅነት በህይወታችን ተጠቃሚዎች ልንሆን ያስፈልጋል።

<u>ማጠቃለያ</u>

ነገረ ማርያም በነገረ ድኅነት በሚል አቢይ ርእስ ሥር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልዑል እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ባደረገው ጉዞ ወይም ነገረ ድኅነት(የሰው መዳን) ሰፊ ድርሻ ይዛ እንደምትገኝ እንዲሁም እመቤታችን ከጥንተ አብሶ (ስውር ኃጢአት) በፍፁም ንፅሕና ቅድስና የተለየች መሆኗንና ኪዳነ አዳም በእርሷ መፈፀሙን እንዲሁም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታ ፅንስ እሰስከ ቀራኒዮ ያደረገችው ፍፁም መንፈሳዊ አገልግሎት የተገለፀ ሲሆን እንዲሁም የእመቤታችን አማላጅነት ከነገረ ድኅነት (ከሰው ልጅ መዳን) ጋር ተያይዞ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ለሰው ከሰጠው ፀጋ አንዱ መሆኑን ለማየት ተሞክሯል፡

<u>ዋቢ መፃሕፍት</u>

1. መፅሐፍ ቅዱስ
2. ወንጌል አንድምታ
3. ነገረ ድህነት በዲ/ን ያረጋል አበጋዝ
4. ወላዲተ አምላክ በመፅሐፍ ቅዱስ
5. ሃይማኖተ አበው
6. ውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ
7. ወላዲተ አምላክ በነገረ ድህነት ዲ/ን አንዱዓለም

ምዕራፍ አራት

ክብረ ድንግል

መግቢያ

በዚህ ምዓረፍ ክብረ ድንግል በሚል ርእስ ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ማለትም የተሰጣት ፀጋ ምን እንደሆነ የምንመለከትበት ነው፡፡ ለማሳየትም እመቤታችን የአምላክ እናት መሆኗን ቅድስናዋን ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን የምንመለከትበት እና በሌላም ንዑስ ርእስ የክብረ ድንግል መገለጫዎች የሆኑትን ማለትም ለአምላክ እናት ለእመቤታችን ስግደት እንደሚገባት ምስጋና እንደሚገባት እንዲሁም በስሟ ዝክር(መታሰቢያ) ማድረግ እንደሚገባ እና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነቷ ቃል ኪዳኗ የተገለፀ ሲሆን ከዚህ የተነሳ ተማሪዎቹ እመቤታችን የአምላክ እናት የመሆኗን ነገር ይመሰክራሉ እመቤታችን በነፍስ በሥጋ በውስጥ በአፋአ ያላትን ቅድስና ያብራራሉ ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ያብራራሉ በህይወታቸውም የእመቤታችን ቃል ኪዳን እና አማላጅነት አውቀው የበለጠ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ለእመቤታችን የሚገባውን ምሥጋና በመረዳት እነርሱ ከበፊት በበለጠ ለማመስገን ይነሳሳሉ፡፡

ጥያቄ

ሀ.ክብረ ድንግል ማርያም ስንል ምን ማለታችን ነው
ለ.ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና የምታውቀውን ያህ አብራራ
ሐ.ስለ እመቤታችን አማላጅነት የምታውቀውን ያህል ግለፅ
መ.ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው

ክብረ ድንግል

4.1.የአምላክ እናት መሆኗ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆኗ ቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው።ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ኢሳይያስ በትንቢቱ እንዲህ ብሎ ተናግሯል “ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶልናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።ኢሳ 9፥6 ይህም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ” ተብሎ የተነገረለት የባህርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።እርሱን የወለደች ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት በሌላም ሥፍራ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሏል “ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ተብሎ ይጠራል”።ኢሳ 7፥14 “አማኑኤል” ማለትም የእግዚአብሔር መልአክ እንደተረጐመው እግዚአብሔር ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነስቶ ሰው ሆነ ማለት ነው ይህም የባህርይ አምላክ ነው በድንግልና ፀንሳ

በድንግልና የወለደችው ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ስለዚህ የአምላክ እናት መባል ይገባታል።ማቴ 1፥23።

ቅድስት ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተመልታ ድንግል ማርያም የአምላክ እናት መሆኗን ስትመሰክር የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል ብላለች።ሉቃ1፥43። ድንግል ማርያም በቅድምና ለነበረ አካላዊ ቃል ለእግዚአብሔር ወልድ እናቱ ናት።ዮሐ 1፥1-14 ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው።የሐዋ.ሥራ 20፥80። ስለዚህም ነው የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ የምንላት በዘመኑ ፍጻሜ ከእርሷ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ አምላክ ወልደ አምላክ ነው።ገላ 4፥4፣ሮሜ 1፥3-4 ስለዚህም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ትባላለች።

በብሉይ ኪዳን ነቢያት "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" እያሉ የተናገሩት ትንቢት በኢየሱስ ክርስቶስ መፈፀሙ የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት የባህርይ አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።ኢዮ 2፥32፣የሐዋ 2፥21-38፣ሮሜ 10፥9-13፣ኢሳ 40፥3፣ማር1፥1-3 እነዚህን ማመሳከሩ ብቻ በቂ ነው።ይህንን ሁሉ ይዘን ድንግል ማርያም ለአምላክ እናትነት ብቻ የተፈጠረች የእግዚአብሔር እናት ናት እንላለን።

በተጨማሪም የእስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ አባታችን ቅዱስ ቄርሎስ "አማኑኤል የባሕርይ አምላክ እንደሆነ ንጽሕት ድንግልም አምላክን የወለደች እንደሆነች ሰው የሆነ የእግዚአብሔርንም ቃል እንደወለደች የማያምን ሰው ቢኖር የተወገዘ ይሁን" በማለት ካወገዙ በኋላ ዳግመኛ በኋላ ዘመን ቅድስት ድንግል እርሱን በሥጋ ወለደችው ስለ እኛ ሰው የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ወለደችው ስለዚህም ቅድስት ድንግልን ወላዲተ አምላክ እንላታለን። ሃ.አበው ገጽ 277-305 በማለት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ መባል እንደሚገባት አስረግጠ ተናግሯል።

4.2. <u>ቅድስናዋ</u>

እመቤታችን ከሁሉ ይልቅ ወላዲተ አምላክ በመሆኗ ከፍጥረታት ሁሉ የከበረች ናት ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጣት ስለሆነችም ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለየች ትባላለች።አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።ዘሌ 19፥2 ብሎ እንደተናገረው በፈጣሪው አርአያና አምሳል ለተፈጠረው የሰው ልጅም በቅድስና የፈጣሪውን አርአያ መከተል ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው።ይህንን ግዴታ ለመፈጸም በቀና እምነትና በበጎ ምግባር ለብፅዕና ለቅድስና የበቁ የብሉይና የሐዲስ ምእመናን ቁጥር በፈጣሪ እንጂ በፍጡር አዕምሮ ተደምሮና ተባዝቶ የሚደረስበት አይደለም ሆኖም ከዚህ ዓለም ቅዱሳን እና ቅዱሳት መካከል እንደ

እመቤታችን ያለ በእርስዋ መጠን ፀጋን የተመላ በንጽሕናና በቅድስና የተዋበ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነና በልዑል ኃይልም የተጠበቀ ሰውነት ያለው የለም።ሉቃ 1፥28-36።

ይኸውም እመቤታችን ለአምላክ እናትነት የተመረጠች ድንግል በመሆኗ እና የአምላክ እናት እንደመሆኗ መጠን በሐልዮ በማሰብ፣በነቢብ በመናገር፣በገቢር በመከወን ንፅሐ ጠባይ ያላደፈባት ቅድስትና ቡርክት በመሆኗ ነው ስለዚህ ራስዋ ወላዲተ አምላክ አስቀድማ በወንጌል ቃል እንደተናገረችው ትውልድ ሁሉ "ቅድስት ወብፅዕት" እያሉ ሲያመሰግኗት ይኖራሉ።ሉቃ 1፥48።

በብሉይና በሐዲስ ኪዳን ማረጋገጥ እንደሚቻለው ለሕይወተ ዓለም እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነው ረድኤተ እግዚአብሔር በዘመነ ፍዳና በዘመነ ኩነኔ ከዓለም ሊርቅና ሊነሳ የቻለው በዓመፅና በክፋት ብዛት ነበር የሰው ልጅ ያን ጊዜ በበረከተ ሥጋ እና በበረከተ ነፍስ እጦት ይሰቃይ የነበረውም በዚሁ ምክንያት ሲሆን ያጣውን ሁሉ አግኝቶ እንደገና ለመክበር የበቃውም ዳግም በፍፁም ተስፋ ይጠበቅ የነበረው የዓለም መሢሕ ከእመቤታችን ከተወለደ ወዲህ ነው።

ስለሆነም የሰው ልጅ ንጽሐ ጠባዩን በድቀተ ኃጢአት ምክንያት ከማደፉ በፊት የነበረው የተፈጥሮ ንጽሐ ሥጋ፣ንጽሐ ነፍስ፣ንጽሐ ልቦና ወይም የሐልዮ፣የነቢብ እና የገቢር ንጽሕና የቱን ያህል እንደ ነበር ማረጋገጥ የተቻለውም በእመቤታችን ንጽሕና ቅድስና ነው፣ይኸውም እመቤታችን ከፈጣሪዋ በተሰጣት ምሉዕ ፀጋ መሰረት በውስጥ በአፍአ የነበራት ንጽሕናና ቅድስና ሁሉ ፍፁም ስለሆነ ነው።እኛም አሁን ከእመቤታችንን ረድኤትና በረከት እንዲከፍለን ወደ ልጅዋ የምንማፀነው በእርስዋ ከተሰጠው የንጽሕናና የቅድስና በረከት እንድናገኝ ነው።

አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአዳም ዘር የተላለፈ ኃጢአት (ጥንተ አብሶ) ያላገኛት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ገና ከመወለዷ አስቀድሞ በአምላክ ሕሊና ታስባ ትኖር የነበረች በሰው ልማድና ጠባይ ከሚደርሰው ሥጋዊ አሳብና ፈቃድ የተጠበቀች፣ከተለዩት የተለየች፣ንጽሕተ ንፁሐን ቅድስተ ቅዱሳን ናት።መኃል4፥7።

"ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ሆይ ደስ ይበልሽ"ተብላ በቅዱሳን መላእክት አንደበት በቅድስናዋ ተመስግናለች።ሉቃ 1፥28።እመቤታችን በውስጥ በአፋአ በነፍስ በሥጋ ቅድስት ስለሆነች እግዚአብሔር ለልጁ ማደሪያ መርጦአታል።ማህደረ መለኮት እንድትሆን አድርጓታል አምላክን ለመውለድ ያስመረጣትና ያበቃት ንጽሕናዋ ቅድስናዋ ነው።አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው "እግዚአብሔር አብ በሰማይ ሆኖ ምሥራቁን እና ምዕራቡን ሰሜኑን እና ደቡቡን ዳርቻዎችን ሁሉ ተመለከተ እንደ አንቺ ያለ አልተገኘም ያንቺን ንጽሕና ወደደ ደም ግባትሽን ወደደ የሚወደውን ልጁን ወደ አንቺ ሰደደ።"ብሏል የእመቤታችን ንጽሕና እና ቅድስና በመወደዱ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፈስ ነስቶ በተዋህዶ ሰው መሆኑን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአምላክ እናትነት መመረጧን የሚያሳይ ነው።ቅዳዊትም በመዝ 131፥13 "እግዚአብሔር ፅዮንን

መርጧታል ማደሪያው እንድትሆን አስጊጧታል።"ብሏል ይህም እመቤታችንን እግዚአብሔር ለእናትነት እንደመረጣት እና በንፅሐ ሥጋ፣በንፅሐ ነፍስ፣በንፅሐ ልቦና እንዳስጌጣት የሚያስረዳ ሀይለ ቃል ነው።

4፥3 **<u>ድንግልናዋ</u>**

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከተለየች የተለዩ፣ከከበሩት የከበረች የሚያደርጋት ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ አምላክን በድንግልና ፀነሳ በድንግልና መውለዷ ነው።ማቴ 1፥18-20።እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ከመፅነሷ በፊት፣በፀነሰች ጊዜ፣ከፀነሰች በኋላ፣ከመውለዷ በፊት፣በወለደች ጊዜ፣ከወለደች በኋላ ድንግል ናት እመቤታችን ከሌሎች ሴቶች ተለይታ እግዚአብሔር ከፈጠራት ጀምሮ በአሳብ በመናገርና በመሥራት ንጽሐ ጠባይ ያላደፈባት ንጽሕት ናት።

"ድንግል" የሚለው ቃል በርግጥ ቅድስናዋን፣ንጽሕናዋን ብቻ ሳይሆን ልዩ መሆኗንም ያመለክታል በዓለም ከነበሩና ከሚኖሩ ሴቶች እንደ እመቤታችን ድንግልና ከእናትነት፣ እናትነትን ከድንግልና አስተባብራ የተገኘች ሴት የለችም እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና ያላት ናት መኃል 4፥15 ነቢዩ ሕዝቅኤል የተመለከተው ራዕይም እመቤታችን እናትና ድንግል መሆኗን ነው።ሕዝ 44፥3።

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ድንግልና እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ወፍ ዘራሽ ብቅ ያለ ሳይሆን ትንቢት የተነገረለት፣ምሳሌ የተመሰለለት አማናዊ ሆኖ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ህይወት የተገለጠ ነው።ትንቢቱን ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ተናግሯል "ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች።"ብሏል።ምሳሌውም ቀዳማዊ አዳም ከጎኑም ምድር ተገኝቷል።ይህም የዳግማይ አዳም ኢየሱስ ክርስቶስ ድንግል ካልሆነች ቢገኝ የቀደመው ከኋለኛው ይበልጣል ያሰኛል።ይህ ደግሞ የሚያንሰው የሚበልጠውን ሊያድን አይችልምና አልዳነም ወደሚል ክህደት ያደርሳል።ስለዚህ እመቤታችን ከዚያችኛዋ ጎኑም ምድር የምትበልጥ ፍፁም ድንግል ናት።

በቅዱስ ወንጌልም ቅዱስ ሉቃስ እንዲህ ብሏል ቅዱስ ገብርኤል "ወደ አንዲት ድንግል ተላከ የዚያችም ድንግል ስም ማርያም ነው።"በማለት ስለ ድንግልናዋ ተናግሯል።ሉቃ 1፥26።ነቢዩ ኢሳይያስም "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች።"ኢሳ 7፥14።በማለት ስምዋን እስከ ግብሯ ድንግል ብሏታል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልናዋ ፀንታ የኖረች የአምላክ እናት ናት ነቢያት የተናገሩት ትንቢትም በእመቤታችን የተፈፀመ እርሷም ዘለዓለማዊ ድንግልና ያላት መሆኗን ወንጌላዊው አረጋግጦ ፅፎታል።ማቴ 1፥18፣ሉቃ 2፥34-35።

ከሊቃውንት መካከልም ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ስለ እመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና እንዲህ ሲል ተናግሯል። “ሥጋ የሌለው እርሱ ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በጌትነቱ ሳለ በማኅፀኗ ተወሰነ።ከዚያ በኋላም የሚወለድበት ቀን ሲደርስ በማይመረመር ግብር በኅቱም ድንግልና ተወለደ ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ተወለደ እንጂ።”ብሏል ሃ.አ ገፅ 212።

“አምላክን የወለደች ማርያም ለዘለዓለሙ ድንግል እንደሆነች መውለዷም የማይመረመር ድንቅ እንደሆነ ከወለደችም በኋላ በድንግልና ፀንታ እንደኖረች አስረዳ” ሲል የተናገረው ደግሞ አባታችን የአንፆኪያው ሊቅ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ሳዊሮስ ነው ሃ.አ.ገፅ 375።

ቅድስት ድንግል ማርያም መድኃኒታችንን ከወለደች በኋላ ድንግል አይደለችም ለሚሉ መናፍቃን መልስ በሰጠበት ድርሳኑ ቅዱስ ጀሮም “ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዘጋው በር እንዴት እንደገባ ይንገሩኝና ቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለዷን እነግራችኋለሁ” ብሏል።(St.mary in the orthodox concept by Tadros malaty).

ስለዚህ የእርሷ የድንግልና ምስጢር በሥጋዊ አዕምሮ ሊደርስባት የማይቻል ድንቅ ነው። ቅዱስ ኤፍሬምም ነቢዩ ሕዝቅኤል የተናገረውን ትንቢት ሲተረጉም እንዲህ ብሏል “ነቢዩ ሕዝቅኤል የመሰከረለት ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ከኃያላኑ ጌታ በቀር ማንም ወደ እርሷ ገብቶ የወጣ የሌለ በምሥራቅ ያያት ደጅ የተባለች መድኃኒታችንን የወለደች ድንግል ናት እርሱን ከወለደች በኋላ እንደ ቀድሞው በድንግልና ኑራለችና መጥቶ ምሕረት ከሌለው ጠላት እጅ ያዳነን ጌታን የወለድሽ ሆይ የማኅፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው።አንቺ ፍፅምትና የተባረክሽ ነሽ የእውነት አምላክ በሆነ በክብር ባለቤት ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና በምድር ላይ ከሚኖሩ ሁሉ ይልቅ ገናንነትና ክብር ላንቺ ይገባል።”በማለት በረቡዕ ውዳሴው አመስግኗታል።እኛም የድንግልናዋን ነገር በአንክሮ እያሰብን ለምኝልን ልንላት ያስፈልጋል።

4.4. <u>የክብረ ድንግል መገለጫዎች</u>

ክብር የሚለው ቃል ጌትነትንና ከፍተኛነትን የሚያሳይ ነው።ከሁሉ በላይ ክብር ያለው እግዚአብሔር ነው:: ክብሩም በሥራው ይታያል።መዝ 18፥1፣ዘፀ16፥7፣ኢሳ6፥3።እግዚአብሔር ክቡር በመሆኑ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ቅድስት ድንግል ማርያም አንዳች ያልጎደለባት ምልዕተ ጸጋ ስለሆነች እግዚአብሔርም ከእርሷ ጋር ስለሆነ ክብርት ናት።እንኳን መልዕልተ ፍጡራን የሆነች እርሷ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ክቡር ነው።ሉቃ 2፥9፣1ቆሮ 11፥7፥1ቆሮ15፥41።

አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብሩን በተአምራቱ በደብረ ታቦር በትንሣኤውና በዕርገቱ ገልጧል።ዮሐ 2፥11፣ማቴ 17፥1፣1ጴጥ 1፥20 በኋላም በዳግም ምጽአቱ ይገለጣል።ማር 8፥38።የእናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ደግሞ የተገለጠው አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና በመውለዷ ነው።ይህ ክብር ልዩ ነው።ምክንያቱም ከእርሷ በቀር የአምላክ እናት የሆነ የለምና ወደ ፊትም አይኖርም።

እመቤታችንን አስቀድሞ ያከበራት ልዑል እግዚአብሔር ነው።ነቢያትም እግዚአብሔር በገለጠላቸው መንገድ በትንቢት መነፅር እያዩዋት ክብሯን ተናግረውላታል።የምሥራቹን ይነግራት ዘንድ ወደ እርሷ የተላከ ቅዱስ ገብርኤልም አብስሯታል።ቅድስት ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ አነቃቅቷት የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ አይገባኝም ብላ አክብራታለች ዮሐንስም በራዕዩ "ፀሐይን ተጐናፅፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራስዋ ላይ አሥራ ሁለት ከዋክብት የሆነላት"። በማለት ክብሯን በሰማይ ከፍ ብሎ በማየቱ አክብሯታል።ከነቢያት ለመጥቀስ ያህል ንግሥቲቱ በወርቅ ልብስ ተጐናፅፋና ተሸፋፍና በቀኝህ ትቆማለች ያለው የእመቤታችንን ክብሯን ሲገልጥ ነው።ራዕ 12፥1፣መዝ44፥9።ቤተ ክርስቲያናችን የእመቤታችንን ክብር ስለምታውቅና ስለምታምን ለምዕመናን ሁሉ የድንግል ማርያምን ክብር ታስተምራለች ምዕመናንም ይህንን አውቀው ያከብሯታል።

አባታችን ቅዱስ ኤፍሬምም በረቡዕ ውዳሴው "ከቅዱሳን ክብር የማርያም ክብር ይበልጣል የአብን ቃል ለመቀበል በተገባ ተገኝታለችና።መላእክት የሚፈሩትን ትጉሆች በሰማያት የሚያመሰግኑትን ድንግል ማርያም በማህፀኗ ተሸክማዋለች እርሷ ከኪሩቤል ትበልጣለች ከሱራፌልም ትበልጣለች ከቅድስት ሥላሴ ለአንዱ ማደሪያ ሆናለችና የነቢያት ሀገራቸው ኢየሩሳሌም ይህቺ ናት።ለቅዱሳን ሁሉ የደስታቸው ማደሪያ ናት ሲል የተሰጣትን ክብር ገልጧል እኛም ቅዱስ ኤፍሬምን አብነት አድርገን እመቤታችንን ቅድስት ድንግል ማርያምን እናከብራታለን።

4.4.1 <u>ስግደት ለእመቤታችን</u>

የእመቤታችን ክብር (ማክበራችንን) ከምንገልጥበት መንገድ አንዱ ለእመቤታችን የሚገባ "የፀጋ ስግደት" ነው።አንዳንድ ሰዎች (ከሃይማኖት ውጭ የሆኑ) ለእመቤታችን የምናቀርበውን "የፀጋ ስግደት" ልክ ለአምልኮ (ለእግዚአብሔር ብቻ የሚሰገድ) ስግደት አድርገው ሲነቅፉት ይሰማሉ።አርቶዶክሳዊ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ግን ለእመቤታችን የምታቀርበው ስግደት የፀጋ (የአክብሮት) ስግደት እንጂ የአምልኮት ስግደት አይደለም በእርግጥ የአሰጋገድ ሥርዓታችን ስንሰግድ ማለትም ለእግዚአብሔር የአምልኮት ለእመቤታችን የፀጋ ስግደት አንድ አይነት የሆነ ቢመስልም አምላካችን እግዚአብሔር ነገርን ሁሉ ስናደርግ አስቀድሞ ልባችንን የሚያይ በመሆኑ

ዋናው ነገር ስግደቱን የሚያቀርበው ሰው ሕሊናው እና ልቡናው ነው።ስለዚህም ለእመቤታችን የፀጋ (የአክብሮት) ስግደት፣ለአምላካችን ለልዑል እግዚአብሔር የአምልኮ ስግደት እናቀርባለን።

ለእመቤታችን የፀጋ ስግደት መስገድ እንዲገባ ቅዱሳት መጻሕፍት ተባብረው አስረግጠው ተናግረዋል።ኢሳ 49፥22። “ወንዶች ልጆችሽንም በጫንቃቸው ላይ ይሸከሟቸዋል።ነግስታትም አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ።እቴጌዎቻቸውም ሞግዚቶችሽም ይሆናሉ ግንባራቸውንም ወደ ምድር ዝቅ አድርገው ይሰግዱልሻል የእግርሽን ትቢያ ይልሳሉ”። ብሎ ነቢዩ ቅዱስ ኢሳይያስ አስቀድሞ ተናግሯል በሌላም ስፍራ ነቢዩ እንዲህ ብሏል “የእግሬን ሥፍራ እሰብራለሁ የአስጨናቂዎችም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ የእግዚአብሔር ከተማ የእሥራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል።ኢሳ 60፥13።

መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም በሐዲስ ኪዳን ገና በእናቱ በቅድስት ኤልሳቤጥ ማኅፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተመላ ስለነበር የእመቤታችንን ድምፅ ለኤልሳቤጥ በተሰማበት ቅጽበት የፀጋ ስግደት ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም የአምልኮት ስግደት በማኅፀነ ድንግል ላለው ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰግዷል።ይህን ያስደረገ መንፈስ ቅዱስ ነው።ዛሬም የእግዚአብሔር መንፈስ ያልተለየው ሁሉ ለእመቤታችን ክብር ይንበረከካል ይሰግድለታልም።ሉቃ 1፥15፣ሉቃ1፥39-46።

4.4.2.<u>ምስጋና ለእመቤታችን</u>

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቀደም ብለን እንደገለፅነው ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች በዚህም የአምላክ እናት የሆነች በአማላጅነት በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል የምትቆም ንጽሕት ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን ሁሉ በላይ የከበረች ማህደረ መለኮት በመሆኗ ከባህርይ አምላክ ቀጥሎ የፀጋ ምስጋና ይቀርብላታል።በቤተ ክርስቲያናችን በመዝሙራችንም ሆነ በቅዳሴያችን ከስመ ሥላሴ ቀጥለን የምንጠራው የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ስም ነው።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በብሉይ ኪዳን ክብሯ እና ልዕልናዋ በነቢያት ሲነገር የኖረ በሐዲስ ኪዳንም ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም በቀር “ደስ ይበልሽ ፀጋ የመላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ” ተብሎ የተመሰገነ ማንም አልነበረም ሉቃ 1፥28። ሰማያውያን መላእክት ቅዱስ ገብርኤልን አብነት አድርገው ያመሰግኗታል።ደቂቀ አዳም ደግሞ እንደ ቅዱስ ገብርኤል ባለ ምስጋና እንድታመሰግን መንፈስ ቅዱስ ገልያላት እመቤታችንን ያመሰገናች ቅድስት ኤልሳቤጥን አብነት አድርገን

እናመሰግናታለን። “በኤልሳቤጥ መንፈስ ቅዱስ መላባት በታላቅ ድምፅ ጮሀ አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽ ፍሬም የተባረከ ነው” አለች እንዲል።ሉቃ 1፥39-45።

እመቤታችን እራሷ “ከእንግዲህ ወዲህ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል” ብላ ተናግራለች (ሉቃ 1፥48)። ይህም ማለት ትውልደ ሴም፣ትውልደ ካም፣ትውልደ ያፌት ንዕድ ነሽ ክብርት ነሽ እያሉ ያመሰግኑኛል ማለቷ ነው።ከዚህ የወጣ ትውልድ የለምና እንዲህ ብላ በተናገረችው መሰረትም በልጇ የመንን ኦርቶዶክሳዊያንም መመኪያ ዘውዳችን ጥንተ መድኃኒታችን የንፅህና መሠረታችን ድንግል ማርያም ናት ብለን እናመሰግናታለን።

አምላካችን እግዚአብሔር ለወዳጁ ለአብርሃም “ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፣እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ።ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።ዘፍ 12፥1-3። ብሎታል ከዚህ የእግዚአብሔር ቃል የምንማረው የቅድስተ ቅዱሳን የድንግል ማርያም ስም ክቡር መሆኑንና ብናመሰግናት በረከትን እንደምናገኝ ብንነቅፋት መርገምን እንደምንቀበል ነው።ምክንያቱም እመቤታችን የአብርሃም ዘር ነች አንድም እመቤታችን የአብርሃምን አምላክ የወለደች ለአብርሃም የተነገረው ተስፋ ሁሉ የተፈፀመባት ስለሆነ ከአብርሃም ትበልጣለች ስለዚህ ለእመቤታችን ምሥጋና ይገባታል።

ለእመቤታችን ምስጋና እንደሚገባ ከላይ ለመመልከት እንደ ምክር ነው:: ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝተው እመቤታችንን ካመሰገኑ ምስጋናቸው በመፅሐፍ ተፅፎ ከሚገኙ ሊቃውንት መካከል የጥቂቶቹን እንመለከታለን።

ሀ.<u>አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ</u>፦ይህ ቅዱስ የእመቤታችን ፍቅር ያደረበት በመሆኑ በሰዓታት ድርሰቱ እመቤታችንን በሰፊው አመስግኗል ለአብነት ያህልም፦

“እዌድሰኪ ኦ ድንግል ምልእተ ውዳሴ መጠነ ይክል አፍየ አሰተበፅዕ ዕበየኪ ማርያም” ትርጉም ምስጋናን የተመላሽ ድንግል ማርያም ሆይ አመሰግንሻለሁ የአንችን ምስጋና እና ልዕልና አንደበቱ ተናግሮ መፈፀም አይቻለውም።

“ልሳነ ኪሩቤል ኢይክል አብጽሐ ውዳሴኪ ወአፈ ሱራፌል ኢይፈጽም ነጊረ እበየኪ ማርያም” ትርጉም የኪሩቤል አፍ ምስጋናሽን መፈፀም አይቻለውም በሱራፌል አንደበትም ልዕልናሽ ድንቅነትሽ ተነግሮ አያልቅም <u>(ሰዓታት ዘሌሊት)</u>

ውድሰት አንቲ በሰፈ ነቢያት ወሰብሕት በሐዋርያት አክሊለ በረከቱ ለያዕቆብ ወትምክሕተ ቤቱ ለእሥራኤል <u>ትርጉም</u>፦ እመቤታችን ማርያም ሆይ በነቢያት እና በሐዋርያት አንደበት

ትመሰገኛለሽ ለአባታችን ለያዕቆብ የበረከቱ ዘውድ አንቺ ነሽ ለእሥራኤል ዘሥጋ ለእስራኤል ዘነፍስ መመኪያቸው አንቺ ነሽ።

ለ.<u>አባ ሕርያቆስ፡-</u> ይህ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝቶ ለእመቤታችን የቅዳሴ ድርሰት የደረሰ ሲሆን ይህ ቅዳሴው በሙሉ የእመቤታችንን ክብር፣ልዕልና፣ቅድስና፣ድንግልና የሚመሰክር ነው። ለአብነት ያህልም

"ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናብየኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዕ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበአማን" <u>ትርጉም</u>፡- ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን እውነተኛ የሕይወት መብልንና እውነተኛ የሕይወት (መጠጥ) ክርስቶስን ወልደሽልናልና

"ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ በመኑ ወበአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ" <u>ትርጉም</u>፡- ምስጋናን የተመላሽ ሆይ በማን እና በምን ምሳሌ እንመስልሻለን?

4.4.3. <u>የእመቤታችን ቃል ኪዳን አማላጅነት እና መታሰቢያ (ዝክር)</u>

በዚህ ክፍለ ትምህርት ሦስት ዓበይት ርዕሶችን ይዞ እንመለከታለን እነርሱም

- ✓ ሀ. የእመቤታችን ቃል ኪዳን
- ✓ ለ. የእመቤታችን አማላጅነት
- ✓ ሐ. በእመቤታችን ስም (ዝክር) መታሰቢያ ማድረግ

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን በጥልቀት ለመመልከት እንሞክራለን።

<u>ሀ.የእመቤታችን ቃል ኪዳን:-</u> "ቃል ኪዳን" ትርጓሜው ውል ስምምነት መሓላ የሚል ሲሆን በቃል ኪዳን ውስጥ ቃል ኪዳኑን ሰጪ፣ቃል ኪዳኑን ተቀባይ፣በቃል ኪዳኑ ተጠቃሚ የሚሆኑ እንዳሉ ያስረዳል ይህን ሀሳብ ግልፅ ለማድረግ ቃል ኪዳን ሰጪ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ሲሆን ቃል ኪዳኑን ተቀባይ እመቤታችን እና ሌሎችንም በተጋድሎ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ ቅዱሳን ናቸው በቃል ኪዳን ተጠቃሚ የሚሆኑት ደግሞ በቅዱሳን በእመብታችን ቃል ኪዳን ይሆንልኛል ብለው ያመኑ ሁሉ ናቸው ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ።መዝ 88፥3 እንዲል።

እግዚአብሔር አምላካችን መዓቱን በምሕረቱ ቁጣውን በትዕግስቱ በመግታት የሰውን ሕይወት ለዘለዓለሙ ለመጠበቅ ሲል በመጀመሪያ በስሕተቱ ከተፀፀተው ከአዳም ቀጥሎ በዓድቅነቱ ከጥፋት ውኃ ለመዳን ከቻለው ከኖህ ከዚያም በእምነቱ በምግባሩ ቀናነት የእግዚአብሔር ወዳጅ ተብሎ ከተሰየመው ከአብርሃም ጋር ለመላው የሰው ዘር ሁሉ የሚሆን የምሕረትና የበረከት ቃል ኪዳን ገብቷል።ዘፍ 9፥11-17 ፣ ዘፍ12፥1።

ልዑል እግዚአብሔር ከዘመነ ብሉይ ቅዱሳን አበው ጋር ገብቶት የነበረው ቃል ኪዳን በአሮሩ ይህ ሲሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ ወዲህ ግን በብሉይ ኪዳን ቅዱሳን እና ቅዱሳት ጋር እንደሆነ በራሱ በሐዲስ ኪዳን ቃል ማረጋገጥ ይቻላል።

ከዘመነ ብሉይና ከዘመነ ሐዲስ ቅዱሳን መካከል ከፍተኛው ፀጋና ክብር የተሰጠውም የአምላክ እናት ለሆነችውና በዚህም "ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች" እየተባለች ለምትጠራው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስለሆነ ሌሎች የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳንና ቅዱሳት ከተሰጠው ቃል ኪዳን ይልቅ ለእመቤታችን የተሰጠው ከሁሉም በላይ የበለጠ /የላቀ/ነው።

ይህንንም ለማረጋገጥ በድቀተ ኃጢአት በተከሰተው የኩነኔ ዘመን መጀመሪያ ላይ ተሰፋ ቅቡዓን መድኃኔዓለም "ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ" ሲል ለአባታችን አዳም የገባውንና በኋላም በተግባር የተገለጠውን የቃል ኪዳን ፍፃሜ መመልከት አስፈላጊ ነው።

"ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ"የሚለው የምሕረት ቃል ኪዳን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአዳም የቃል ኪዳን ልጅ መሆኗን የሚያረጋግጥ ሲሆን መስቀሉን በሞቱ አዳምን ለማዳን ከአዳም የልጅ ልጅ የተወለደው መሢህ ኢየሱስ ክርስቶስ በልደቱ በሞቱ ዓመተ ኩነኔን በዓመተ ምሕረት ለመተካት አስቀድሞ የገባውን ቃል ኪዳን ፈፅሞአል።

በመሆኑም በመልዕልተ መስቀል ስለ እኛ ድኅነት ተሰቅሎ ሳለ በመስቀሉ ስር የልጇን መከራ እየተመለከተች ልብን በሚነካ ሐዘን ስለ ልጇ ታለቅስ የነበረች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እና ይወደው የነበረ ደቀመዝሙሩ ቅዱስ ዮሐንስ ነበሩ ጌታችንም የሚወዳት እናቱን ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ እነሆ ልጅሽ አለ ይህ የተነገረው የአደራ ቃል ደግሞ እመቤታችን በእርግጥ ለሐዲስ ኪዳን ምእመናን የተሰጠች የቃል ኪዳን እና የድኅነት ምክንያት የሆነች እናት መሆኗን ነው ።

ስለሆነም ምን ጊዜም ምእመናን ቅድስተ ቅዱሳን ለሆነችው እናቱ የሰጠውን የምሕረት ቃል ኪዳን በማሰብ በምሕረትና በቸርነቱ ይጎበኛቸው ዘንድ በወላዲተ አምላክ ስም ይማፀናሉ።

- በእንተ ማርያም መሐረነ ክርስቶስ
- እመቤታችን ሆይ ወደ እኛ ተመልከች የልጅሽ ቸርነት ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ
- ቅድስት ሆይ ለምኝልን
- ስለ እናቱ ስለ ወላዲተ አምላክ ብሎ በቸርነቱ ከመዓቱ ይሠውረን እያልን እንማጸናለን የተሰጣትን ኪዳን መማፀኛ እናደርጋለን።

በዚህ መሠረትም እመቤታችን ፀጋን ሁሉ የተመላች የቃል ኪዳን እናት እንደመሆንዋ መጠን በማያሳብል የእናት አማላጅነቷ ጸጋን የምታሰጥ ልዕልተ ምሕረት ስለሆነች በስሟ ተማጎፅኖ ማድረግ እንደሚገባ አበው ያስተምሩናል።

ለ.<u>የእመቤታችን አማላጅነት:-</u> የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ በልብ ወለድ የሚነገር ሳይሆን መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው።መዝ 44፥9። "ንግስቲቱ ወርቅ ዘቦ ግምጃ ደርባ እና ተጎናጽፋ በቀኝህ ትቆማለች በማለት ተናገረ ትቆማለች ማለቱ ለአማላጅነት ነው።ምዕመናን ምግባር ጎድሎባቸው በልጇ ፊት የሞት ሞት የሲኦል ፍርድ እንዳይፈረድባቸው ልጄ ማርልኝ የገባህልኝን ቃል ኪዳን አስብ እያለች በቀደመ ልመናዋ የምታሰማራቸው (የምታግልዳቸው) መሆኑን መናገሩ ነው።

የእመቤታችንም ሆነ የቅዱሳን ምልጃ የታዘዘውና የተፈቀደው (ያስፈለገው) እግዚአብሔር ከጎጥአን ይልቅ የፃድቃን ፀሎት የበለጠ ስለሚሰማ ነው።የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ፃድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸው።መዝ 33፥15።ተብሎ ተፅፎአል አማላጅነት የእግዚአብሔር የቸርነት ስጦታ ነው።ምክንያቱም ምግባራቸው የደከመና ፀሎታቸው እንደርሱ ፈቃድ ያልሆኑ ተነሳሕያን ኃጥአን የእርሱን ፈቃድ በሚያውቁ እና በሚፈፅሙ በምግባር በበለፀጉ ቅዱሳን ይልቁንም በእናቱ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም በኩል እንዲረዱ ማድረግ የቸርነቱ መገለጫ ነው።

ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም የምእመናን ሁሉ "እናት" ሁና መሰጠቷን ቅዱስ ወንጌል ምስክር ሆኗል።ዮሐ19፥26። የእናት አማላጅ ደግሞ አያሳፍርም ምክንያቱም የሰራኝታዋ መበለት ልጅ በሞተባት ጊዜ ለእግዚአብሔር ሰው ለኤልያስ ነግራ (አማልዳ) ከሞት እንዲነሳ አደረገች።1ነገ 17፥17-24።ሌሎችም ብዙ እናቶች ለልጆቻቸው ብዙ ነገር አድርገዋል ርብቃ ለያዕቆብ በጥበብ የአባቱን በረከት አሰጥታዋለች።ዘፍ 25፥ ከነቢያት ወገን የሆነች ሴት ባሏ በዕዳ የተበደረውን ሳይከፍል ቢሞት ልጆቿ በባርነት እንዳይያዙባት ለነቢየ እግዚአብሔር ለኤልሳዕ ነግራ ጥቂቱን ዘይት አበርክቶላት ያንን ሸጣ ዕዳዋን ከፋላ ልጆቿን ከባርነት ነፃ አውጥታለች 2ነገ 4፥25። በከነዓን ትኖር የነበረችው ሴትም ልጇ እንድትፈወስላት ለጌታችን ነግራ ለዚያውም ጌታችን "በውሻ" መስሏት ግን በትህትና ቃል "ውሾችም ከጌታቸው ማዕድ የሚወድቀውን ፍራፋሬ ይመገባሉ።" በማለት የሚያራራ የልመና ቃል አቅርባ ልጇ እንድትፈወስላት ሆናለች።አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው እንደ እምነትሽ ይደረግልሽ ባላት ጊዜ ልጇ ተፈወሰች።እንዲል ማቴ15

ስለዚህ ከእንተም የምትበልጥ እናት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ምንም ምሳሌ የማይገኝላት እመቤታችን ታማልደናለችና በህይወታችን በአማላጅነቷ ሁል ጊዜ ልንጠቀም ያስፈልጋል።በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ልጅዋ መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ውኃውን ወደ ወይን

ለውጠ የመጀመሪውን ተአምር ያደረገው በእመቤታችን አማላጅነት ነው።ዮሐ2፥1-11።ውሃ ጣዕም መልክ የለውም በእመቤታችን አማላጅነት ግን ወይን ሆኖ መልክ ጣዕም አመጣ እንደዚሁ ሁሉ የክርስትና መልክ የክርስትና ጣዕም በህይወታችን እንዲኖር የእመቤታችን ምልጃ ወሳኝ ነገር መሆኑን የዚህ ክፍለ ንባብ ታሪክ ያስረዳናል።

በቤተ ክርስቲያናችን እምነት እና ትምህርት ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ከስመ ሥላሴ ቀጥሎ ስሟ የሚጠራ ስለሆነ ታማልዳለች ብለን ማመናችን ቢያንስ እንጂ ሊበዛ አይችልም።

- እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሁሉ ቃል ኪዳናቸውን በመጠበቅ ከእነርሱ ጋር ለዘለዓለም ይኖራልና (መዝ 88፥3።)የማማለድ ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል።
- ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አግኝተሻልና አትፍሪ ብሎ መልአኩ በክብር እንዳበሰራት እንረዳለን።ሉቃ1፥28-30።"ሞገስ" የሚለው ቃል ባለሟልነት፣ክብር፣ተሰሚነት፣ማማለድ፣ማስታረቅ የሚሉትን ያብራራል:: ይህ ሁሉ ለእመቤታችን የተሰጠ ፀጋ ነው።

እንግዲህ ከብዙው በጥቂቱ ስለ እመቤታችን አማላጅነት ለመግቢያ ያህል ከላይ የተዘረዘሩትን ከተመለከትን ትልቁና ዋነኛው ነገር በዕለት ተዕለት ኑሮአችን በአጠቃላይ በህይወታችን በእመቤታችን አማላጅነት የበለጠ ተጠቃሚዎች ለመሆን ልንተጋ ያስፈልጋል።አባቶቻችን በብሒላቸው የእናት አማላጅ ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ ሲሆን በውድ አለበለዚያ በግድ ይላሉ እና በእመቤታችን አማላጅነት የልጇ ቸርነት እንዲደረግልን ልንተጋ ያስፈልጋል።

<u>ሐ.በእመቤታችን ስም መታሰቢያ (ዝክር)</u>

<u>ማድረግ</u>

በኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም የክብር መገለጫ ከሆኑት ነገሮች መካከል በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ሥም ዝክር መዘከር ነው:: "ዝክር" ትርጓሜው መታሰቢያ ማለት ሲሆን ይህ ዘለዓለማዊ መታሰቢያ ለወዳጆቹ ለቅዱሳን ይልቁንም ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም እንዲደረግ የፈቀደ አምላካችን ልዑል እግዚአብሔር ነው። "እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላል::በቤቴና በቅጥር ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ ኢሳ 56፥4እና5 እንዲል።

ጌታችንም በቅዱስ ወንጌል “ፃድቅን በፃድቅ ስም የተቀበለ የፃድቁን ዋጋ ያገኛል እውነት እላችኋለሁ በቀደ መዝሙሩ ስም ቀዝቃዛ ፅዋ ውሃ የሰጠ ዋጋው አይጠፋበትም” ማቴ 10፥41::ብሎ እንደተናገረ በፃድቃን በቅዱሳን ስም የተመፀወተ (የተሰጠ) የማይጠፋ ዘለዓለማዊ ዋጋ የሚያሰጥ ከሆነ የፃድቃን የቅዱሳንን አምላክ የወለደች የእመቤታችንን ስም ለሚጠራ የሚመፀውትማ የበለጠ ዋጋ ይሰጠዋል ማለት ዋጋው አይጠፋበትም።

ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በተአምረ ማርያም መቅድም እንደተጻፈ በሕግ የተወሰኑ 33 በዓላት አሏት::እነዚህን በዓላት ምክንያት አድርገን በስሟ የተራበ ልናበላ የተጠማ ልናጠጣ የታረዘ ልናለብስ የተጨነቀ ልናረጋጋ ለቤተ ክርስቲያን ዕጣን ጧፍ፣ዘቢብ የተለያዩ ንዋየ ቅድሳት ልንሰጥ በአጠቃላይ በጎ ሥራ ልንሰራ ያስፈልጋል:: ይህንን በጎ ሥራችንን ወደ ልጇ አቅርባ የኃጢአት ሥርየት ታሰጠናለች፡በኋላም እረፍት መንግስተ ሰማያት ታኖረናለች።

ጌታችን በቅዱስ ወንጌል እንዲህ ብላል “ምሳ ወይ እራት ባደረግህ ጊዜ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት እንዳይጠሩህ ብድራትህንም እንዳይመልሱልህ ወዳጆችህና ወንድምችህን ዘመዶችህንም ባለጠጎች ጎረቤቶችህንም አትጥራ ነገር ግን ግበግ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ በፃድቃን ትንሣኤ ይመለስልሀልና።”ሉቃ 14፥12-14።እንዲል።

ማጠቃለያ

ክብረ ድንግል በሚል አቢይ ርእስ እመቤታችን የአምላክ እናት መሆኗን ዘለዓለማዊ ድንግልና እንዳላት ከተለዩ የተለየች ቅድስተ ቅዱሳን መሆኗን እንዲሁም ለእመቤታችን የክብር መግለጫ የሚሆኑ ስግደት ምሥጋና እንደሚገባት በስሟ ዝክር ማድረግ እና አማላጅነቷን በመታመን በህይወታችን መጠቀም እንደሚገባን ለማሳየት ተሞክሯል።።የበለጠ በዚህ ዙሪያ የተፃፉ መፃህፍትን መመልከት እና አባቶችን መጠየቅ ይገባል።።

ዋቢ መፃህፍት

1. መጽሐፍ ቅዱስ
2. ሃይማኖተ አበው
3. ወላዲተ አምላክ በመፅሐፍ ቅዱስ
4. ወላዲተ አምላክ በነገረ ድህነት ዲ/ን አንዱአለም
5. ወላዲተ አምላክ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪን መ/ር ሮዳስ

ምዕራፍ 5

ስለ እመቤታችን የተመሰለ ምሳሌ እና ትንቢት

መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአበው ቀደምት የተመሰለላት ምሳሌ እና በቅዱሳን ነቢያት የተነገረላትን ትንቢት እንመለከታለን፡፡በዚህም ውስጥ ምሳሌ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና በምሳሌ መስለው ማስተማርም መፅሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን እና የሚገባ መሆኑን እንመለከታለን፡፡እንዲሁም ትንቢት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነቢያት የተነገሩ ትንቢቶች እንዴት እንደሚተረጎሙ የምንመለከትበት የነገረ ማርያም ትምህርት ምዕራፍ ነው፡፡

ጥያቄ

ሀ.ምሳሌ ማለት ምን ማለት ነው?
ለ.በምሳሌ ማስተማር ይገባልን?
ሐ.ስለ እመቤታችን የምታውቀውን ምሳሌ ተናገር?
መ.ትንቢት ማለት ምን ማለት ነው?
ሰ.ስለ እመቤታችን ነቢት ከተናገሩት ትንቢት የምታውቀውን ግለፅ?

ስለ እመቤታችን የተመሰለ ምሳሌ እና ትንቢት

5.1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በአበው ቀደምት የተመሰለላት ምሳሌ

- ምሳሌ ማለት ምን ማለት ነው?

5.1.1. **ምሳሌ**፡- ምሳሌ አንድን ነገር ግልጥ ለማድረግ ሲፈለግ የሚቀርብ ማስረጃ ማብራሪያ እና መግለጫ ነው።

ምሳሌ፡- አንድ ነገር አማናዊ ሁኖ ከመምጣቱ በፊት የሚቀርብ ነው።

ምሳሌ፡- አንድ ነገር እንዳይረሳ ያደርጋል በይበልጥም ያብራራል ሰው እንዲያስብበት ይቀሰቅሳል።

ምሳሌ፡- አስተዋዮችን ልባም ያደርጋቸዋል የማያስተውልቱን ግን በድንቁርና ያጨልማል።ለዚህ ነው ጌታችን የዘሪውን ምሳሌ ከተናገረ በኋላ “የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ” በማለቱ በዙሪያው የነበሩት ከአሥራ ሁለቱ ጋር ስለምሳሌው ሲጠይቁት “ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል በውጭ ላሉት ግን አይተው እንዳያዩ እንዳይመለከቱም ሰምተውም እንዳይሰሙ

እንዳያስተውሉም እንዳይመለሱም ኃጢአታቸውም እንዳይሰረይላቸው ነገር ሁሉ በምሳሌ ይሆንባቸዋል" አላቸው።ማር 4፥12

<u>ምሳሌ</u>፡- የተመሰለ ምሳሌያት ትርጓሜም አላቸው <u>ለምሳሌ</u>:- በማቴ 13፥30-43 በቅዱስ ወንጌል የተነገረውን ምሳሌ ለሐዋርያት ተተርጉሞ እንመለከታለን።

ከላይ ለመግቢያ ያህል ስለ ምሳሌ ምንነት ይህንን ከተመለከትን በምሳሌ መስሎ ማስተማር የተመሰለውንም መተርጎም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ነው በዘመነ ብሉይ ጠቢቡ ሰሎሞን መፅሐፍ የተፃፉ ብዙ ምሳሌዎችን አስተምሯል::1ነገ 4፥32በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በብዙ ምሳሌ አስተምሯል:: "በምሳሌ አፌን እከፍታለሁ" ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ።መዝ 77፥1 እንዲል::ጌታችን ያለ ምሳሌ አላስተማረም በምሳሌ ካስተማረም በኋላ ነገሩን ሁሉ ለገዛ ደቀ መዛሙርቱ ይፈታላቸው ይተረጉምላቸው ነበር::ማር 4፥33::ስለዚህ እውነተኛ ትርጉም የሌለው ምሳሌ እንደሌለ እንማራለን።

በቅዱስ መፅሐፍ ስለ ጌታ ስለ እመቤታችን ስለ ቤተ ክርስቲያን ወዘተ የተመሰለ ምሳሌዎች አያሌ ናቸው አስተዋይ የሆነ ትርጓሜአቸውን በመረዳት ይጠቀምባቸዋል።በመፅሐፍ ቅዱስ ስለ እመቤታችን የተነገሩትን ምሳሌዎች በመመርመርና ትርጓሜያቸውን እንድናስተውል ያስፈልጋል በተለይ የብሀንሳው ኤጲስ ቆጳስ አባችን አባ ሕርያቆስ በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝቶ በቅዱስ መፅሐፍ የተፃውን የእመቤታችንን ምሳሌ በመግልፅ እመቤታችንን አመስግኗታል።ስለዚህ እኛም ለትምህርታችን የተመሰለ ጥቂት ምሳሌዎችን ተርጉመን እንመለከታለን።እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ምስጢሩን እና ማስተዋሉን ይግለፅልን አሜን።

ሀ.<u>የኖህ መርከብ</u> ዘፍ 7፥2-23

ኖህ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሊመጣ ካለው ጥፋት ለመዳን መርከብን አዘጋጀ እርሱ ሚስቱ እና ሴም ካም ያፌት የተባሉ ልጆቹ ከነ ሚስቶቻቸው ከየወገኑም የተመረጡ እንስሳት ሁሉ ወደ መርከቧ ገቡ በዚህም ከጥፋት ውኃ ዳኑ::ዘፍ 7፥2-23:: "ኖህ ገና ስለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተሰቦቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ በዚህም ዓለምን ኮነነ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ::ዕብ 11፥7::እንዲል ኖህ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ያገኘ በትውልዱ ጻድቅ ፍፁምም ሰው ነበር አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ፈጣሪው የሚድንበትን መንገድ አሳው በዚያም ተጠቅሞ 3 ክፍል ባላት መርከብ ለመዳን በቃ በኖህ ያላገጡ በተዘጋጀው መርከብ እንድናለን ብለው ያላመኑ ጠፉ ይህ እንግዲህ ምሳሌ ነው።የምሳሌውም ትርጓሜ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

- የኖህ መርከብ:- የእመቤታችን ምሳሌ ናት ሦስት ክፍል እንደነበራት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የአብ ሙሽራው የወልድ እናቱ የመንፈስ ቅዱስ ንፅሕት አዳራሽ ናትና

አንድም እመቤታችን በንፅሐ ሥጋ በንፅሐ ነፍስ በንፅሐ ልቡና የተሸለመች ቅድስተ ቅዱሳን የመሆኗ ምሳሌ።

- ኖህ:- የጌታ ምሳሌ
- የጥፋት ውሃ:- የምልአተ ኃጢአት ምሳሌ <u>አንድም</u>:- የሲኦል ምሳሌ
- ከመርከብ ውስጥ ሁነው ከጥፋት የዳኑ:- በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን እና አማላጅነት ያመኑ በእርሷም ምልጃ ከጥፋት የዳኑ ከሲኦል የሚድኑ ነፍሳት ምሳሌ
- ከመርከብ በአፍአ በስተውጭ የቀሩትና የጠፉት:- በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን እና አማላጅነት ሳያምኑ በኃጢአት በሲኦል የጠፉት የሚጠፉት ነፍሳት ምሳሌ
  - ከኖህ ሕይወት የምንማረው ነገር አለ እርሱም ፃድቅ ፍፁም እንደሆነ እየተመሰከረለት ነገር ግን አምላካችን እግዚአብሔር ለመዳን የሚሆንለትን መርከብ እንዲያዘጋጅ ሲያዘው አልተከራከረውም በእምነት መርከብ ሰርቶ በመርከብ ከጥፋት ዳነ እንጂ ስለዚህ በእኛ ዘመን አንዳንድ ሰዎች በሌላቸው ፅድቅ እየተመፃደቁ የእመቤታችንን ቃል ኪዳን እና አማላጅነት አያስፈልግም በማለት ሲንቁ ይታያል እኛ ኦርቶዶክሳውያን ግን እንደ ኖህ አባታችን የተሰጠችንን የመዳን ምክንያት እመቤታችንን ማለትም አማላጅነቱን በህይወታችን ሁልጊዜ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል የእመቤታችን አማላጅነት አይለየን አሜን!

ለ.<u>የአብርሃም ድንኳን</u>

በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ አድባር ዛፍ ተገለጠለት ዓይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቁመው አየ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነስቶ ሮጠ ወደ ምድርም ሰገደ እንዲህም አለ አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ ባርያህን አትለፈኝ::ዘፍ 18፥1-5::

ቅዱስ አብርሃም በዚህ ምድር ቤት አልነበረውም የሚኖረው በድንኳን ነበርና በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሥላ በሰው አምሳል ተገለጡለት እነሆ ለእርሱ በሃይማኖት ሥላሴ መሆናቸው ተገለጠለት ስለነበረ በግንባሩ ተደፍቶ የአምልኮት ስግደት ሰገደላቸው በአክብሮትም ተቀበላቸው ወደ ድንኳንም እንዲገቡ በባለማልነቱ ተማፀናቸው አስተናገዳቸውም ሥላሴ ወደ አብርሃም ድንኳን ገብተው ተስተናግደውለታል::በዚህ ክፍለ ንባብ እና ታሪክ ውስጥ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን በምሳሌነት ከዚህ እንደሚከተለው እናገኛታለን::

- አብርሃም ድንኳን:- የእመቤታችን ምሳሌ ምክንያቱም ሥሉስ ቅዱስ በማህጸኗ አድረዋልና ይኸውም አብ ለማፅናት ወልድ ለመፀነስ (ሰው ለመሆን) መንፈስ ቅዱስ ለመጋረድ ስለዚህ ማህደረ ሥሉስ ቅዱስ ትባላለች::
  - አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ በማግኘቱ ነው::ሥላሴ ወደ ድንኳኑ ገብተው የተስተናገዱት እመቤታችን ማህደረ ሥሉስ ቅዱስ ለመሆን የተመረጠችው በእግዚአብሔር

ፊት ሞገስ በማግኘቷ ነበር የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል እንደመሰከረው ::ሉቃ1፥28ኳ::

<u>ሐ.የሲና ሐመልማል ዕፅ ጳጦስ</u> **ዘፀ3፥1-6**

ሙሴም የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር ወደ ምድረ በዳም ዳርቻ በጎቹን ነዳ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው እነሆም ቁጥቋጦው ስለምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራዕይ ልይ አለ እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ ሙሴ ሙሴ ሆይ አለ እርሱም እነሆኝ አለ ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምክባት ስፋራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው ደግሞም እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ አለው ሙሴም እግዚአብሔርን ያይ ዘንድ ፈርቷልና ፊቱን ሸፈነ::ዘፀ 3፥1-6 በዚህ ንባብ በምሳሌነት የእመቤታችን ነገር እንማራለን::

- ዕፀ ጳጦስ (ሲና ሐመልማል)፡-የእመቤታችን ምሳሌ
- ነበልባሉ፡- የመለኮት የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ
- ሐመልማሉ፡- የትብስዕት የሥጋ ምሳሌ
- ነበልባሉ እና ሐመልማሉ ተዋሕደው ሙሴ መመልከቱ፡- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የመውለዳ ምሳሌ
- ደብረ ሲና፡- የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት::ሙሴ ጫማህን አውልቅ እንደተባለ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጫማ አድርጎ መግባት አይገባም ሲል ነው::

<u>መ.የኢያሱ የምስክርነት ሐውልት</u> **ኢያ 24፥25-27**

በዚያ ቀን ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ በሴኬምም ሥርዓትና ፍርድ አደረገላቸው ኢያሱም ይህን ቃል ሁሉ በእግዚአብሔር ሕግ መጻሐፍ ጻፈ ታላቁንም ድንጋይ ወስዶ በእግዚአብሔር መቅደስ አጠገብ ከአለችው ከአድባሩ ዛፍ በታች አቆመው ኢያሱም ለሕዝቡ እነሆ የተናገረንን የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ሰምታልና ይህ ድንጋይ ይመሰክርብናል እንግዲህ አምላካችሁን እንዳትክዱ ይህ ይመሰክርባችኃል አላቸው::ኢያ 24፥25-27::እንዲል ኢያሱ የተካላት የምስክርነት ድንጋይ ሐውልት እስራኤል ከሞዓብ አማልክት ይልቅ እግዚአብሔርን መርጠው ቃል የመግባታቸው ምልክት ነበር ድንጋይቱም ሦስት ገፅ ነበራት

- ሐውልቲቱ፡- የእመቤታችን
- ሦስት ገፅ መሆንዋ፡- እመቤታችን በሥጋዋ፣በነፍስዋ፣በሕሊናዋ፣ድንግል መሆኗ ምሳሌ አንድም እመቤታችን የቅድስት ሥላሴ ማደሪያ ለመሆኗ
- ❖ ሐውልቷ የኢያሱ የስሙ መታወቂያ ነበረች፡- ኢያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው:: የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስም መታወቂያው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት ጌታ በዚህ ዓለም የታወቀው የተገለጠው የታየው ከእርሷ ተወልዶ ነውና ያለ እመቤታችን ጌታን አውቀዋለሁ ማለት አስቸጋሪ ነው::የአንድን ወንዝ ምንነት ለማወቅ ወደ ምንጩ መሄድ አስፈላጊ ነው

ሰ.<u>የኤልያስ የወርቅ መሶብ</u> **1ኛ ነገ 19፥1-10**

ነቢዩ ኤልሳዕ ከንጉሥ አክአብና ከንግሥት ኤልዛቤል በተጣላ ጊዜ ነፍሱን ለማዳን አንድ ቀን የሚያህል መንገድ ሄደ በምድረ በዳ በክትክታ ዛፍ ሥር ተኝቶ ሳለ መልአኩ የተጋገረ እንጎቻና በማሰሮ ውሃ አምጥቶ ሁለት ጊዜ እንደመገበውና በዚያም ኃይል አግኝቶ እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀን አርባ ሌሊት እንደ ተጓዘ ቅዱስ መጽሐፉ ይነግረናል::1ነገ 19፥1-10::በዚህ ታሪክ ውስጥ የእመቤታችንን ነገር የሚገልጥ ምሳሌ እናገኛለን::ምሳሌውም:-

- ኤልያስ፡- የአዳም እና የልጆቹ የምዕመናን ምሳሌ
- መሶበ ወርቅ፡- የእመቤታችን ወርቅ የንፅህናዋ የቅድስናዋ ምሳሌ
- መና፡- የጌታ ምሳሌ <u>አንድም</u>:- የሥጋ ወደሙ::ዮሐ 6፥51
- እንቅልፍ፡- የኃጢአት ምሳሌ
- መልአኩ፡- የካህናት የመምህራን ምሳሌ

ነቢየ ኤልያስ በመልአኩ መቀስቀስ ከእንቅልፉ ነቅቶ ዳግመኛ በተመገበው ምግብ ኃይል አግኝቶ እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ እንደተጓዘ ሁሉ የሰው ልጅም ዳግመኛ በተሰጠው የሕይወት ምግብ በሥጋውና በደሙ ኃይል አግኝቶ ወደ መንግሥተ ሰማያት የመግባቱ ምሳሌ ነው::

ታላቁ አባት ቅዱስ ኤፍሬምም የተሰወረ መና ያለብሽ የንፁህ ወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ መናም ከሰማይ የወረደውና ለዓለም ሁሉ ሕይወትን የሚያድለው ሕብስት ነው::በማለት አመሰጠረ /ውዳሴ ዘሰንበት/::

ከላይ በጥቂቱ ስለምሳሌ እና ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም በቅዱስ መፅሐፍ የተመሰሉት እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም ከተመሰሉት ምሳሌዎች እና ትርጉማቸው በጣም ጥቂት እና ለማሳያ እንደ መግቢያ የሚሆኑ ናቸው መምህሩ የበለጠ ሌሎችንም ጨምሮ ለተማሪዎቹ (ለሰልጣኞቹ)ማስረዳት ማሳየት ይችላል::

5.2. <u>እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቅዱሳን ነቢያት የተነገረላት ትንቢት</u>

- ትንቢት ማለት ምን ማለት ነው?

<u>ትንቢት</u>፡- የሚመጣውን ማናቸውንም ነገር አስቀድሞ የሚገልጥ ነው::ዕብ 1፥1

<u>ትንቢት</u>፡- ከመፈፀሙ በፊት እንዴት እንደሚፈፀም አይታወቅም ከተፈፀመ በኃላ ግን ድርጊቱ የትንቢቱ ፍፃሜ መሆኑን የእግዚአብሔር ሰዎች ያስተውላሉ የእግዚአብሔር ያልሆኑ ግን አያስተውሉም የአዲስ ኪዳን ፀሐፊዎች “በነቢይ የተባለው ይፈፀም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆነ” እያሉ ደጋግመው ብሉይ ኪዳንን ጠቅሰዋል:: ማቴ 1፥22፣1ጴጥ 1፥10::

<u>ትንቢት</u>፡- ትርጓሜ አለው የትንቢትን ቃል መተርጎም ከባድ ነው::በመሆኑም ማንም እንደመ ሰለው ይተረጉም ዘንድ አልተፈቀደለትም:: "ይህንን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደለትም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ተነድተው ተናገሩ እንጂ"እንዲል 2ጴጥ 1፥20::

<u>ትንቢት</u>፡- እንደ መሰረታዊው ዓላማው እንጂ ቃል በቃል ላይፈፀም ይችላል::**ለምሳሌ:-**በት.ሚል 4፥5 ላይ የተነገረው ትንቢት ስለ ኤልያስ የተተነበየው በመጥምቁ ዮሐንስ ተፈፅሞአል::ማቴ 17፥10::መሠረታዊው ነገር ሕዝብን ለእግዚአብሔር ማዘጋጀት ነው:: በዚሁ ምሳሌ ኤልያስ ተብሎ በዮሐንስ እንደ ተተረጎመ ሁሉ "ጽዮን" ተብሎ በትንቢት መፅሐፍ የተነገረው በእመቤታችን ተፈፅሞአል::

- ስለ ትንቢት ምንነት ለግንዛቤ ያህል በጥቂቱ ከላይ ከተመለከትን ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከተነገሩ ትንቢቶች ለትምህርታችን ጥቂቶቹን ብቻ እንመለከታለን አምላካችን ይግለጽልን አሜን !

ሀ. ሰው እናታችን ጽዮን ይላል
በውስጧም ሰው ተወለደ
እርሱ ራሱም ልዑል መሰረታት:: <u>መዝ 86፥5</u>

→ ይህንን የትንቢት ቃል በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም የተናገረው ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ነው::ነቢዩ በትንቢቱ "ሰው እናታችን ጽዮን ይላል" ብሎ "በጽዮን" አንፃር ስለ እመቤታችን የተናገረው ነው:: "ጽዮን" ማለት አምባ፣መጠጊያ፣ ለጠላት የማትበገር፣ማለት ሲሆን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ፀወነ ኃጥአን ወፃድቃን ፀወነ ሥጋ ወነፍስ ናት ለጠላት ዲያብሎስ አሳልፋ የማትሰጥ የምዕመናን ወዳጅ አማላጅ በመሆኗ "ጽዮን" መባል ይገባታል:: ነቢዩ ቅ.ዳዊት እናታችን መባል እንዲገባትም ተናግራል በእውነት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዮሐንስ ወንጌላዊ አማካኝነት የተሰጠችን በመሆና ሁል ጊዜ እናታችን እንላታለን::ዮሐ 19፥26::

"በውስጧ ሰው ተወለደ":- ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ይሄ የትንቢት ቃል ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የባህርይ አምላክ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ፍፁም አምላክ፣ ፍፁም ሰው፣ ሁኖ እንደሚወለድ የተናገረው ነው::

→ "እርሱ ራሱም ልዑል መሰረታት":- ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ከእርሷ የተወለደው ልዑለ ባሕርይ ::ኢየሱስ ክርስቶስ በንፅህና በቅድስና በዘለዓለማዊ ድንግልና እንዳፀናት (እንደመሰረታት) መሰረት ያለው ነገር ሁሉ እንደማይናወፅ እርሷም ሁከት ሥጋዊ እንዳሌለባት በመንፈስ ቅዱስ ተቀኝቶ ስለ እመቤታችን ተናገረ::

ለ. በወርቅ ልብስ ተጎናፅፋና ተሸፋፍና ንፍሥቲቱ

በቀኝህ ትቆማለች ልጄ ሆይ እዩ ጆሮሽንም አዘንብይ

ወገንሽን የአባትሽን ቤት እርሺ

ንጉሥ ውበትሽን ወዷልና እርሱ ጌታሽ ነውና መዝ 44፥9

ልበ አምላክ የተባለ ዳዊት በትንቢቱ "ንግሥት" ያላት ቅድስት ድንግል ማርያምን ነው ነቢዩ ዳዊት ከዘጠኝ መቶ ዘመን በኋላ ቅድስት ድንግል ማርያም ከእርሱ ወገን ከእርሱ ዘር እንደምትወለድ በእግዚአብሔር መንፈስ ተረድቶ "ልጄ ሆይ" ብሎም ጠርቷታል::

→"ንጉሥ" ያለው:- የባሕርይ አምላክ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

→"ውበትሽን"ያለው:- ደግሞ ንጽሕናዋን፣ቅድስናዋን ፣ድንግልናዋን ነው::

አንድም

→"ወርቀ ዘቦ ደርባ ደራርባ ለብሳ ተጎናፅፋ ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች" አለ:- በወርቀ ዘቦ ግምጃ ምሳሌነት የተነገረለት የእመቤታችን ንጽሐ ሥጋ፣ንጽሐ ነፍስ፣ንጽሐ ልቡና ነው:: ንጽሐ ሥጋ፣ንጽሐ ነፍስ፣ንጽሐ ልቡና አንድ አድርጋ እመቤታችን በሰጠሀት ክብር ትፀናለች ማለቱ ነው::በቀኝህ ትቆማለች ማለቱ ታማልዳለች ማለቱ ነው::

→"ንጉሥ ውበትሽን ወዳልና":- ንጉሥ ክርስቶስ ንጽሕናሽን ቅድስናሽን ወዶ ለእናትነት መርጦሻልና ማለቱ ሲሆን

→"ወገንሽን የአባትሽን ቤት እርሺ":- ማለቱ በዚህ በተነገረ ትንቢት ምክንያት አብርሃም ከአገሩ እንደወጣ ከአባቷ ቤት ወጥታ አብርሃም ከዘመዶቹ እንደተለየ ገና በሦስት አመቷ ከወገኖቿ ተለይታ መላእክት እያረጋጓትና እየመገቧት በቤተ መቅደስ የመኖሯ ነገር ተገልያለት ሲሆን ምስጢሩ ግን እንደ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ የምትወልጂ አይደለሽም እንበለ ዘር በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በንፅሕና፣በቅድስና፣በድንግልና እንጅ ማለትም የእመቤታችን ጌታን መውለድ የተለየ መሆኑን በትንቢት መናገሩ ነው::

ሐ. እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ

ወደ ግብፅ ይመጣል የግብጽም ጣዖታት

በፊቱ ይርዳሉ የግብፅም ልብ በውስጧ ይቀልጣል ኢሳ19፥1

→ይህንን የትንቢት ቃል ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ኢሳይያስ የተናገረው ሲሆን በዚህ ትንቢት የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን እና የልጇን የመድኃኔ ዓለም ክርስቶስን የስደታቸውን

ነገር ወደ ግብፅ እንደሚደረግ እና በግብፅ የሚመለኩ ጣያታት እንደሚቀጠቀጡ /እንደሚጠፉ/ የተናገረው ትንቢት ነው ኃይለ ቃሉም እንደሚከተለው ይተረጎማል::

"እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ ወደ ግብፅ ይመጣል":- "ፈጣን ደመና" ያላት:- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ነው:: "አፍጣኒተ ረድኤት ማርያም በጊዜ ምንዳቤ ወአፀባ ለአይን እምቀራንባ" እንዳለ ደራሲ ትርጉሙም:- እመቤታችን ማርያም ሆይ በመከራ /በችግር/ ጊዜ ረዳትነትሽ ከአይን ርግብግቢት ይፈጥናል ማለት ነው:: "ፈጣን ደመና" እመቤታችን መሆኗን ቅዱስ ወንጌል ሲያስረዳ በሉቃ ም 1፥39 ላይ "በዚያ ወራት ማርያም ፈጥና ወደ ተራራማው ሐገር ወደ ይሁዳ ወጣች" ብሏል::

⟶"እግዚአብሔር በፈጣን ደመና እየበረረ" ማለቱ:- ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው የሆነ ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልደ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ "እግዚአብሔር" እንደሆነ ተናገረ::ክብር ይግባው እና ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማያምኑ መልስ ሰጠ::

⟶"ወደ ግብፅ ይወርዳል" አለ:- አምላካችን ክርስቶስ ከእመቤታችን በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ ይዘው መምጣታቸውን ተመልክቶ ንጉሥ ሄሮድስ በምቀኝነት ጌታን ሊገድለው ተነሳ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክም ለአረጋዊ ዮሴፍ በሕልም ተገልፆ ህፃኑን እና እናቱን ወደ ግብፅ ይዞ እንዲሸሽ /እንዲሰደድ/ አዞታል::ሄሮድስም እስኪሞት ሦስት ዓመት ከስድስት ወር በዚያ ተቀምጠዋል ይህ እንደሚፈፀም ተገልፆለት አስቀድሞ ነቢዩ ኢሳይያስ የተናገረው ትንቢት ነው::ማቴ 2፥13-19::

⟶"የግብፅ ጣያታት በፊቱ ይርዳሉ" :-ይህም ጌታችን እመቤታችን ዮሴፍና ሰሎሜ በስደት ወደ ግብፅ በገቡ ጊዜ ተፈፅሞአል ጣያታቱ ተደምስሰዋል::ግብፅም ከአምልኮ ጣያት እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ተመልሳለች በዚህም ምክንያት ታላላቅ ገዳማት እና ደብረ ቁስቋም እና ደብረ ምጥማቅ ወ.ዘ.ተ::ተገኝተው የቅዱሳን መኖሪያ ሆነዋል::ይህ ይፈፀም ዘንድ እንዳለው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለቅዱስ ኢሳይያስ ገልፆለት የተናገረው ነው::

መ. ወደ ምሥራቅ ወደ ሚመለከተው በስተውጭ ወደ አለው ወደ
መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር::እግዚአብሔርም ይህ
በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና
ተዘግቶ ይኖራል::ሕዝ 44፥1እና2::

ስለ ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ቅድስናና ክብር በትንቢታቸው ከመሰከሩ ቅዱሳን ነቢያት መካከል አንዱ ነቢየ እግዚአብሔር ሕዝቅኤል የተናገረው ትንቢት ነው::የትንቢቱም ኃይለ ቃል እንዲህ ይተረጎማል:-

- ምሥራቅ ያላት:- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት::

- መቅደስ ያለው:-ማኅፀናን ነው::
- የተዘጋው በር:-ያላት ማኅተመ ድንግልናዋን ለመግለጥ ነው::
- ተዘግቶ ነበር:-ሲል ጌታን ከመውለዷ በፊት ድንግል እንደነበረች
- ተዘግቶ ይኖራል አይከፈትም:-ማለቱ መድኃኔዓለም ክርስቶስን ከወለደች በኋላ በዘለዓለማዊ ድንግልና ፀንታ መኖራን ያስረዳል::

"ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና" የሚለው ኃይለ ቃል :- ወላዲተ አምላክ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ከወለደችው በኋላ በዘለዓለማዊ ድንግልና ፀንታ የምትኖር መሆኑን እና ከጌታ በቀር ሌላ ልጅ እንደሌላት በማያሻማ ቋንቋ ያረጋገጠበት ትንቢታዊ መነፅር ነው::

- ❖ እመቤታችን ለማመስገን ታላቅ ፀጋ የተሰጠው አባት ቅዱስ ኤፍሬምም እንዲህ ብላል "ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ እርስዋ /እመቤታችን/ መሰከረ ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ደጅ በምሥራቅ አየሁ አለ::ከኃያላን ጌታ በቀር ወደ እርስዋ ገብቶ የወጣ የለም" ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ
- ❖ ከላይ በጥቂቱ ያየነው ስለ "ትንቢት" እና ስለ እመቤታችን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱሳን ነቢያት የተናገሩት ትንቢት እነዚህ ብቻ ናቸው::ማለት አይደለም ከተነገሩት ትንቢቶች መካከል በጣም ጥቂት እና ለማሳያ እንደ መግቢያ የሚሆኑ ናቸው::መምሕሩ የበለጠ ሌሎችንም ጨምሮ ለተማሪዎቹ (ለሰልጣኞቹ) ማስረዳት ማሳየት ይችላል::

<u>ማጠቃለያ</u>

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ወፍ ዘራሽ በሐዲስ ኪን ብቅ ያለች ሳትሆን በብዙ ደጅ ፅናት አበው ቀደምት ምሳሌ የመሰሉላት ነቢያት ትንቢት የተናገሩላት መሆኗን ከብዙ በጥቂቱ ለማየት ተሞክሯል፡፡ስለዚህ ከዚህ በመነሳት የበለጠ በዚህ ዙሪያ የተፃፉ መፃህፍትን በማንበብ እና አባቶችን በመጠየቅ የበለጠ ትምህርቱን ማዳበር ይገባል፡፡

<u>ዋቢ መፃህፍት</u>

1. ውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ
2. ወላዲተ አምላክ በመፅሐፍ ቅዱስ
3. ወላዲተ አምላክ በሐዲስ ኪዳን እና በብሉይ ኪዳን መ/ር ሮዳስ
4. "ነገረ ማርያም" በማኅበረ ቅዱሳን

ማጠቃለያ

የነገረ ማርያም ትምህርት ዋና ዓላማ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ያላትን ሥፍራ ማሳየት እና ከእርሷ የተነሳ ማለትም ከቅድስናዋ የተነሳ እግዚአብሔር ሰው ለመሆን እንደ መረጣት እና በእርሷ የሰውን ማንነት (ሥጋ) እንዳከበረው ተረድተን ሕይወታችንን በቅድስና እንድንጠብቅ ሲሆን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ በቅድስና ሕይወት ለመኖር ራሳችንን ከተለያዩ ፈተናዎች ለመጠበቅ በምናደርገው የቅድስና ተጋድሎ ውስጥ ረዳትነትዋን በማመን መማፀን እንደሚገባ የበለጠ ለማወቅ እና በሕይወታችን ለመጠቀም እንድንችልና ነቢያት በትንቢት አበው በምሳሌ ሲመስሉና ሲናፍቅዋት የነበሩትን እናት እኛ በእግዚአብሔር ቸርነት በመስቀል ላይ በእናትነት ስለተቀበልናት እንደ ቅዱስ ዮሐንስ በቅርበት በእናትነትዋ መጠቀም ይገባል::የድንግል ማርያም አማላጅነት የልጇ ቸርነት የቅዱሳን ፀሎት የመላእክት ተራዳኢነት አይለየን አሜን!

ዋቢ መጻሕፍት

1.ወንጌል አንድምታ

2.መፅሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጉሙ ቅዳሴ ማርያም

3.ሃይማኖተ አበው

4.ውዳሴ ማርያም እና ቅዳሴ ማርያም አንድምታ

5.ቀሲስ እሸቱ ታደሰ እና ቀሲስ ደጀኔ ሽፈራው ወላዲተ አምላክ በመፅሐፍ ቅዱስ

6.ነገረ ማርያም ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል

7.ወላዲተ አምላክ በብሉይ ኪዳን እና በሐዲስ ኪዳን መምህር ሮዳስ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር